# ዕርቀሰላም፡- የቱለማ ኦሮሞ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስልት መቋጫ

**በገናናው ከተማ[1] እና ታደሰ በሪሶ[2]**

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የቱለማ ኦሮሞን ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስልት መተንተን ነው፡፡ በዚህ መሰሉ የሰላም ፍኖት አቀራረብ እራሱን ችሎ የተሰራ ጥናት አላገኘንም፡፡ ይኸውም አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለጥናቱ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ቀዳማይ እና ካልዓይ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ ቀዳማይ መረጃዎቹ በምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይትን የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን በገላጭ ስልት የተቃኘ ነው፡፡ የተጠቀሱትን ስነዘዴዎች ለጥናቱ መመልከቻነት ከመረጥናቸው ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፎች ጋር በማቀናጀት የጥናታችንን ዓላማ ከግብ አድርሰናል፡፡ በዚሁ መሠረት በኅብረተሰቡ ዘንድ ዕርቅ እና ሰላም (Araara fi naga'a) ለማስፈን ባህላዊ የሽምግልና፣ ሽነቻ፣ ቂጤ (Qixxee) እና የጉማ ሥርዓት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በዚህ ጥናት ተመላክቷል፡፡ እነዚህን የግጭት አፈታት ስልቶች ውጤታማ ለማድረግ  እንደ "ቦኩ፣ ከለቻ እና ጫጩ" ያሉ የከበሩ ንዋያት የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ በተለይም የጉማ ሥርዓትን ካለ ከለቻ እና ጫጩ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ የሀገር በቀል እውቀት ውጤት የሆኑት እነዚህ የኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስልቶች ዋና ማጠንጠኛቸው እውነት፣ ግባቸውም ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ስለሆነ ከዕርቅ በኋላ የጥላቻ እና የበቀል ስሜትን አጥፍቶ በፍቅር እና በሰላም አብሮ ለመኖር ጉልህ ድርሻ እንዳላቸውም የጥናቱ ማጠቃለያ ያሳያል፡፡ ከጥናቱ የመነጨ ይሁንታም ቀርቧል፡፡

**ቁልፍ ቃላት:-** ኦሮሞ፣ የገዳ ሥርዓት፣ ዕርቀሰላም፣ ቦኩ፣ ከለቻ

## 1.መግቢያ

ባህል የሰውን ልጅ ማንነት፣ አኗኗር፣ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ሀብቶች በጥምረት የሚያንፀባርቅ ሲሆን የአንድ ኅብረተሰብ አባላት የሚረከቧቸውን የተጠራቀሙ እውቀቶች፣ እምነቶች፣ ኪነጥበባት፣ መመሪያዎች፣ አርማዎች፣ አመለካከቶች፣ ማህበራዊ ክንውኖች፣ ባህርያት፣ ተቋማት፣ ስነምግባራት፣ ህግጋት፣ ወጎች፣ ልማዶች እና ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁሳዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውሁድ ነው፡፡ ይህም አይነቱ ባህል በማኅበረሰቡ ህሊና፣ በቋንቋና በስነጽሁፍ ተቀርፆ የሚገኝ ሲሆን በኅብረተሰቡ አባላት በግል እና በቡድን ይተገበራል (Geertz, 1993[3]፡ 14; የራስወርቅ፣ 2004 ዓ.ም፡ 3፤ ኃይለገብርኤል፣ 2007 ዓ.ም፡ 1 ፤ ስንቅነሽ፣ 2007 ዓ.ም፡ 32)፡፡

---

1 በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ እጩ ተመራቂ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡ genanawkt@gmail.com
2 ፕሮፌሰር፣ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም አአዩ፡ taddesse.berisso@aau.edu.et
3 'ዓ.ም' የተሰኘውን ምህፃረ ቃል የሌለው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር፤ ያለው ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር የተጠቀሰ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

Tylor (1993፡ 1) በበኩላቸው፣ ከላይ የቀረበውን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ ባህል ወይም ስልጣኔ ሰው እንደ ማኅበረሰብ አባልነቱ ያገኘውን (የሚማረውን/ የሚወርሰውን) ዕውቀት፣ እምነት፣ ጥበብ፣ ግብረገብነት፣ ህግ፣ ልማድ እንዲሁም ማንኛውንም ዓይነት ችሎታ እና ልምድ የሚያካትት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በሁለንታናዊ ብያኔው ባህል ኅብረተሰቡ ያለውን ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ሀብት፣ ማህበራዊ እሴት እና አመለካከት እንዲሁም የሚያከናውናቸውን ማናቸውንም ክስተቶች ጭምር ይመለከታል፡፡ ባህል ሲባል በውስጡ የሚገኙት ዘርፎች እና አከዋወናቸው ብዙ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የቱለማ ኦሮሞ[4] በኅብረተሰቡ ዘንድ በተለያየ ምክንያት የሚከሰቱትን ግጭቶች ለመፍታት የሚጠቀምበትን ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስልት መተንተን ነው፡፡ ንዑሳን ዓላማዎችም አሉት፡፡ እነርሱም፡- የግጭት አይነቶችን እና መንስኤዎችን ማብራራት፣ የግጭት አፈታት ስልቶቹን አከዋወን ፍሬያማ ለማድረግ እና ዘላቂ ሰላምን ከማስፈን አንፃር የከበሩ ንዋያት[5] ያላቸውን ጠቀሜታ መግለፅ፣ የከበሩ ንዋያቱን ማህበራዊ እና ትዕምርታዊ ፍቺ ማሳየት የሚሉት ናቸው፡፡ የጥናቱ ወሰንም የግጭት አፈታት እና የከበሩ ንዋያቱን ምንነት፣ አሰራር፣ አገልግሎት እና ትዕምርተዊ ፍቺ መተንተን ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ከቦታ አንፃር ቱለማ የሰፈረባቸውን ይልቁንም ደግሞ የግጭት አፈታት እና የከበሩ ንዋያቱ ማህበራዊ ፍቺ በምልዓት በሚገኝበት ምሥራቅ ሸዋ፣ ከምሥራቅ ሸዋም በቢሾፍቱ ከተማ ዙሪያ፣ የዱግዳ፣ የቦራ እና የቦሰት ወረዳዎች አካባቢ የተወሰነ ነው፡፡ የጥናቱ ጠቀሜታም በግጭት አፈታት እና በከበሩ ንዋያቱ ዙሪያ ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት፣ የኅብረተሰቡን የታሪክ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ጠንቅቆ ለመረዳት፣ ተመሳሳይ ለሆኑ የኢትኖግራፊ እና የኅብረተሰብ ጥናቶች በመረጃ ምንጭነት ያገለግላል፡፡ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ታሳቢ በማድረግ የተካሄደው ይህ ጥናት በውስጡ የተለያዩ ንዑሳን ርዕሶችን ይዟል፡፡ ተከታዩ ርዕስ የጥናቱን ስነዘዴ የተመለከተ ነው፡፡

## 2. የጥናቱ ዘዴዎች

ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች እና የአተናተን ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርገናል፡፡ ስነዘዴው ከጥናቱ ዓይነት ይጀምራል፡፡

**የጥናቱ ዓይነት፡-** በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ የግጭት አፈታት ስልቶችን እንዲሁም ከግጭት አፈታት ስልቶቹ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውን የከበሩ ንዋያት ለማጥናት በመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ያገኘናቸውን የፎክሎር መረጃዎች ለመፈከር ዓይነታዊ የምርምር ስልትን፣ ከዓይነታዊ የምርምር ባህሪ አንፃርም ጥናቱ ገላጭ ተንታኝ አካሄድን ተከትሏል፡፡

---

4 የቱለማ ኦሮሞ በሀገሪቱ እምብርት ወይም በመሐል ኢትዮጵያ ሰፊ የሆነ አካባቢ ላይ ሰፍሮ ይገኛል (ዓለማየሁ፣ 1998፡ 140)፡፡

5 የከበሩ ንዋያት በተናጥል "የከበረ ንዋይ/ Ulfaa"፣ በወል "Ulfaalee/ የከበሩ ንዋያት" ይሰኛሉ፡፡ ስለ ምንነታቸው እና ክብራቸው በመረጃ አቀባይ የተሰጠውን ገለፃ "ለዕርቅ መቋጫነት የሚያገለግሉ የከበሩ ንዋያት" በተሰኘው ንዑስ ርዕስ ውስጥ ይመለከቷል፡፡

ዘዴው የተመረጠበት ምክንያት የዕርቅ መቋጫ ስልቶቹ እና የከበሩ ንዋያቱ በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ ምን ዓይነት ውክልና እና ፍቺ፣ ጠቀሜታ እንዳላቸው ለመግለጽ የሚረዳ በመሆኑ ነው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከመስክ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ እና ከቤተመጻሕፍት ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ተጠቅመናል፡፡ በመስክ ቆይታ በቃለ ምልልስ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎችን ሰብስበናል፡፡ ከትዕምርት ምንነት እና ጠቀሜታ ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሃሳባዊ ብያዊና ንድፈ ሃሳባዊ መረጃዎችም ተሰብስበው የትንታኔው አካል ሆነዋል፡፡

ከትዕምርት አንፃር ለተሰበሰቡት መረጃዎች ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት ያስችለን ዘንድ የገዳ ሥርዓት እና የዋቄፈና እምነት በሚከወንበት ሥፍራ በተለይም በቢሾፍቱ እና አካባቢዋ (የሦስቱ ቱለማዎች የከበራ ማዕከላት) በመሄድ የህዝቡን እና የአባ ገዳዎችን አኗኗር፣ የርስ በርስ ማኅበራዊ መስተጋብሮችን፣ ዕርቀሰላም የሚከናወንባቸውን ባህላዊ ችሎቶች በማስመልከት ምልከታ አድርገናል፡፡ በዚሁ አግባብ ከህብረተሰቡ ጋር የቆየንባቸው ቀናት በመጀመሪያው ዙር ከጥር 10 እስከ የካቲት 05/06/2010ዓ.ም፣ በሁለተኛው ዙር ከግንቦት 25 እስከ ሰኔ 05/10/ 2010ዓ.ም፣ በሦስተኛው ዙር ከነሐሴ 11 እስከ መስከረም 25/02/2011ዓ.ም፣ በአራተኛው ዙር ከመስከረም 01 እስከ 27/01/2012 ዓ.ም፣ በአምስተኛው ዙር ከጥር 12 እስከ 19/05/2012ዓ.ም ድረስ፣ እንዲሁም ለተጨማሪ የቡድን ውይይት ከመጋቢት 15 እስከ 20/07/2013ዓ.ም በመሐል በመሐልም ልዩ ልዩ ከበራዎች በሚኖሩበት ወቅት በመገኘት በምልከታ ያገኘናቸውን መረጃዎች ለትንታኔው አውለናል፡፡

ቃለ መጠይቅ ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ጥናቱ የተደራጀ እና ያልተደራጀ የቃለመጠይቅ ዘዴን በጥምረት በ ማቀናጀት የተጠቀመ ሲሆን፡ በዚህ ዘዴም ስለ የቱለማ ገዳ ሥርዓት ዕርቀሰላም እና የዕርቅ መቋጫ  ስለሆኑት የከበሩ ንዋያት በደንብ ያውቃሉ የሚባሉ ሰዎች (የባህሉ አዋቂዎች) በጥንቃቄ ተመርጠውና ጥናቱን ለማሳካት የተዘጋጁ ጥያቄዎች በመደበኛ ጊዜ በማቅረብም እንዲመልሱ አድርገናል፡፡ ያልታቀዱ ጥያቄዎችንም በኢ-መደበኛ ጊዜ በመጠየቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ለአባ ገዳ፣ ለአባ ቦኩ፣ ለአባ ሙዳ፣ ለሀደ' ሲንቄ እንዲሁም ለባህሉ ቅርበት ላላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች አቅርበን አስፈልገውን መረጃ በመሰብሰብ ተንትነናል፡፡

"የተተኳሪ ቡድን ለምርምር እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ወይም ስትራቴጂ ሊታይ ይችላል  -Focus groups can be viewed as a data collection method or as a strategy for research" (Mertens, 2015: 450)፡፡ በዚሁ መሠረት በቃለ ምልልስ እና በምልከታ ከተገኙ መረጃዎች መካከል አጥጋቢ ያልሆኑ የተወሰኑ ጉዳዮችን በመለየት ይበልጥ ለማጥራት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተደርጓል፡፡ ዘጠኝ የወንድ መረጃ አቀባዮችን አንድ ቡድን፣ በተመሳሳይ ዘጠኝ የሴት መረጃ አቀባዮችን ሁለተኛ ቡድን በ14/01/2012ዓ.ም በጂሌ፣ ዘጠኝ አባላት ያሉትን ወንድ እና ሴት መረጃ አቀባዮችን በመቀላቀል ደግሞ በ16/07/20013 ዓ.ም በጨፌ ቱማ ሦስተኛውን የቡድን ውይይት በማድረግ የተጣራ መረጃ በመሰብሰብ ለትንታኔያችን ለመጠቀም ተችሏል፡፡

የናሙናው አመራረጥ የፎክሎርን መረጃ ለማግኘት ተመራጭ የሆነውን ዓላማ ተኮር የተከተለ ነው፡፡ ይህንኑ መነሻ በማድረግ ለመረጃ አቀባይነት የተመረጡት ሰዎች የቱለማ ገዳ ሥርዓትንና አወቃቀሩን፣ ትዕምርቶቹንና ፍቺያቸውን ጠንቅቀው ያውቃሉ የሚባሉ አባ ገዳዎች፣ ሃዩዎችና አዛወንቶች፣ ሀደ ሲንቄዎች፣ በዕድሜ ገፋ ያሉ እናቶች፣ ወጣቶች፣ የቢሮ ሠራተኞች፣ የታሪክ መምህራን እንዲሁም የባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች፣ በአካባቢው ላይ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን (አጥኚዎች)... ስብጥሩን በጠበቀ ሁኔታ የመረጃ ምንጮች ሆነዋል፡፡ ከጥናቱ ዓላማ በመነሳት የተሰበሰበው መረጃ በቱለማ ኦሮሞ ገዳ ሥርዓት ውስጥ የግጭት አፈታት ስልት እና የዕርቅ መከወኛ የሆኑትን የከበሩ ንዋያት ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ለጥናቱ መመልከቻነት የቀረቡትን ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳብዊ ማዕቀፎች እንዲሁም ዘዴዎች ጋር በማዋሃድ ትንታኔ አካሂደናል፡፡

## 3. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ዳሰሳ፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተካሂዷል፡፡

### 3.1. ፅንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

#### 3.1.1 ትዕምርት

ትዕምርት (Symbol) ለፎክሎር/ ለባህል ጥናት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ፅንሰ ሃሳብ ሲሆን ሰው፣ ቁስ፣ ኩነት፣ ምልክት፣ ዓርማ ወዘተ. አንድን ዓይነት ቁስ እና ሁኔታን ይወክላል፡፡ ውክልናውም እንደ ማህበረሰቡ ባህል፣ ታሪክ እና ማህበራዊ ፍቺ ሊለያይ ይችላል፡፡ ነጭ ቀለም ብዙውን ጊዜ በምዕራባውያን ባህል የንፅህና ትዕምርት ነው፡፡ ማንዴላ በደቡብ አፍሪካውያን... ዘንድ የፀረ አፓርታድ ትግል ትዕምርት ነው (Hornbay, 2010፡ 1569; Smeets, 1982:17)፡፡

ትዕምርት አንድን ነገር ወይም ቁስ የሚወክል ሲሆን ለፎክሎር ጥናት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ትዕምርት የቁሱን ውክልና የሚያጎላ፣ ምልክታዊ ትርጓሜ የሚሰጥበት ነው፡፡ ቁሶች፣ ምልክቶች እና ልዩ ልዩ ትዕምርቶች የሚተነተኑበት ሲሆን፣ ትዕምርት የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ፣ ፍልስፍና እና የዓለም አተያይ፣ እውቀት እና ጥበብ፣ እምነት እና ኃይማኖት የመሳሰሉትን መነሻ በማድረግ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሃሳብን እንደሚይዝም በጽሑፉ ተመልክቷል፡፡ በዚህም ሳቢያ ትዕምርት የሁለት ነገሮች ጥምረት ነው፡፡ አንደኛው በዓይን የሚታይ እና ተጨባጭ ምልክት (Sensory sign) ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከሚታየው ነገር ጋር የተያያዘው ሃሳብ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች በአንድነት ተጣምረው በባህል ወይም በተለያዩ አውዶች በሚከወኑ ሥርዓተ ከበራዎች፣ ዘፈኖች ወዘተ. ውስጥ ማህበራዊ እና ባህላዊ ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ (Danesi, 2004: 31-32; ሰለሞን፣ 2007፡ 289)፡፡

ትዕምርት እንደ ህብረተሰቡ የተለየየ መልክ እና ዓይነት፣ ቅርጽ እና መጠን አሉት፡፡ የማይታዩ የተባሉት አንድ ትዕምርት የሚወክለውን ሃሳብ የሚመለከት ሲሆን፣

የሚታዩ የሚባሉት ደግሞ በእጅ የሚዳሰሰውን ቁስ የተመለከተ ነው። በሁለቱም ዓይነት ዘርፍ የሚገኙት ትዕምርቶች የሃሳብ፣ የአመለካከትና፣ የፍልስፍና መግለጫ ስልቶች ስለመሆናቸው በጽሑፉ ተብራርቷል። ጥናቱም በዚሁ አግባብ በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ ለዕርቅ መቋጫነት የሚውሉ የግጭት አፈታት ስልቶችን እና ለዕርቅ መቋጫነት የሚውሉ የከበሩ ንዋያትን ገልጿል። ትዕምርታዊ ገፅታቸውንም አሳይቷል። ጥናቱ የ "ዕርቀሰላም" ጉዳዮችን የሚያነሳ በመሆኑ የዕርቅ፣ የሰላም፣ የግጭት እና የግጭት አፈታት ምንነቶች እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

### 3.1.2. ዕርቅ (Araara)

"ዕርቅ ማለት በከባድ ጠብና ይህም ባስከተለው መጎዳዳት ጥለቻ እና መፈራራት ምክንያት ተለያይተው፣ ተራርቀው፣ ተቆራርጠው (alianatod) የነበሩ ሰዎች የጋራ ኑሯቸውን እንደገና ለመገንባት የሚጓዙበት ሂዳት ነው። 'ዕርቅ' የጥልቅ ሰላም ግንባታ ዘዴና ዓለማ ነው" (ሕዝቅያስ፣ 2011፡ 63)። በጥቅሱ መሠረት ዕርቅ የሰላም ሂደት ነው፤ የሰላም መነሻም መድረሻም ነው። የገዳ ሥርዓት ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል ዕርቅ አንዱና ዋነኛው ስለመሆኑ በጥናቱ መግቢያ ተገልጿል። በተመሳሰይ ትርጉም እና ብያኔ፣ "ዕርቅ ግጭትን (አለመግባበትን) በማጥፋት በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያስችል የተከበረ እና መዳበር ያለበት ሁኔታ ሆኖ ይገኛል *-Araarri waldhabbii balleesssanii nagahaan waliin jiraachuu Kan nama dandeechisu haala kabajamaa fi dagaaguu qabu ta'eet argama" (Maammoo, 2002፡103)።*

### 3.1.3. ሰላም (Peace)

ሰላም የዕርቅ ተከታይ ነው። ዕርቅ ከተፈጠረ ሰላም ይሰፍናል፤ ሰላማዊ አኗኗር ይቀጥላል ተብሎም ይታሰባል። በዚህም ሳቢያ ሰላም ዕርቅን ተከትሎ የሚመጣ ክንውን ነው የሚለው ሃሳብ የሚያግባባ ነው።

> *ሰላም የዕርቅ ክንውን የመጨረሻው ውጤት ወይም የተረጋጋ አዝማሚያ ነው። የተጣሉ አልያም የተጋጩ ወገኖች ከብዙ ድርድር እና ንግግር በኋላ ሽምጋዮች በሚሰጡት ዳኝነት ሁለቱም ወገኖች በመስማማት ወደ ቀደመው ህብረት እና አንድነት የሚመለሱበት፣ ሥጋት እና ጦርነት ተወግዶ ደኅንነት የሚታወጅበት፣ መረጋጋት እና ሰላም፣ መከባበር እና መተማመን፣ መግባባት እና ፍቅር የሚነግስበት ድባብ ነው (ዓለሙ፣ 2009 ዓ.ም፡ 161)።*

በሁለንተናዊ ትርጉሙ ሰላም ግጭትን፣ ብጥብጥ እና ጦርነትን በማቆም፣ ዕርቅን በመፈፀም ወደ ቀድሞው መደበኛ እና የተረጋጋ ህይወት መመለስን የሚመለከት ቢሆንም የሰላም ፅንሰ ሃሳብ ግን ሁከትን ከማቆም የሰፋ ጥልቅ ትርጓሜ አለው። ይኸውም ሰላምን የሚነሱ ገሃዳዊ ያልሆኑ ብዙ ዓይት ሁከቶች አሉ፣ "በአንዳንድ ኅብረተሰቦች ውስጥ ጥቂት ሰዎች ከመጠን በላይ ሀብትና ገደብ በሌለው ስልጣንና መብት ሲንፈላሰሱ ብዙሃኑ በድህነትና በጭንቀት፣ በተሰፋ ቢስነት ቀንበር ሥር የሚሰቃይበት ሁኔታ ይታያል" (ሕዝቅያስ፣ 2011፡15)።

በጽሑፉ አገላለፅ መሠረት ድህነት፣ አድሎ እና መገለል፣ ተስፋ መቁረጥ፣ የክብር ማጣት እና መብት መነፈግ የመሳሰሉት እንደ ጦርነት እና ሌሎች የኃይል ስራዎች ጉልህ ሆነው በገሃድ የማይታዩ፣ የረቀቁ እና ስውር ናቸው። በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበረሰብ መዋቅር ላይ የተመሠረቱትን እነዚህን መሰል መገለሎች ሥርዓታዊ ሁከት (structural violence) ተብለው እንደሚጠሩም ጸሐፊው አመልክተዋል። የርዕሰ ጉዳዩ ሀተታ “ሰላም” የሚለው ቃል ጦርነትን ወይም ግጭትን ማቆም ብቻ የተመለከተ ሳይሆን ከማህበራዊ ፍትህ ጋር የተያያዘ ሰፊ እና ጥልቅ ትርጉም ያለው መሆኑን ያሳያል። ለዚህ ደግሞ በከበሩ ንዋያት የታገዘው የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት የዕርቅ አፈፃፀም ስልት በተለያየ አጋጣሚ ለሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሔ ያለው ስለመሆኑ በጥናቱ ተተንትኗል። ለመሆኑ ግጭት ምንድነው?

### 3.1.4. ግጭት (Waldhabbii/ Walitti bu’insa)

እንደ ሰላም ሁሉ ሰፊ እና ጥልቅ ሃሳብን የያዘ ነው። ለብያኔ አሻሚ ከሆኑ ቃላት ተርታ የሚመደብ ቢሆንም በአጠቃላይ ትርጓሜው ግን ልዩነትን፣ አለመግባባትን ያሳያል፣ “ግጭት የሚለው ቃል በልዩነት፣ ባለመስማማት እንዲሁም በተቃርኖ የሚፈጠር ድርጊት ነው። ድርጊቱ ከተራ የቃላት ሽኩቻ እስከ ከፍተኛ እልቂት እና ውድመት ሊደርስ ይችላል” (ዓለሙ፣ 2009፡ 21)። ግጭት የሁለት ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ህዝቦች ወይም ሀገሮች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በአቋም መለያየትን ተከትሎ የሚከሰት መሆኑን የጽሑፉ ሃሳብ ያስረዳል።እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ግጭት ሲኖር ነገሮች ተገቢ ባልሆነ መንገድ እየተከናወኑ መሆናቸውን ለመረዳትም ሆነ መፍትሔ ለመሻት ያስችላል። ግጭትን ለመፋታት የሚቻለው ግጭት ስለመኖሩ በአግባቡ ስንረዳ መሆኑንም ጸሐፊው ገልፀዋል። ለዚህም ደግሞ ግጭት ሁሌም ከሰው ጋር ያለ ስለመሆኑ ይነገራል፣ “የሰው ልጅ ማህበር ፈጥሮ ሥርዓት አበጅቶ በዚህ ዓለም መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ግጭትም አብሮት ኖሯል” (ሙልጌታ፣ 1997፡29)።

ግጭት ወደድንም ጠላንም በሰዎች መካከል ሁል ጊዜ ያለ ነገር ነው። የሚያስከትለውን መጥፎ ውጤት በማሰብ ብቻ ብንሸሸውም እንደ ጥላችን ይከተለናል ያሉት ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ “በአንዳንድ ሰዎች እጅ ግጭት ለመጎዳዳት እና ለመጠፋፋት መነሻ ሲሆን በአንዳንድ ብልህ ሰዎች ዘንድ ግን ችግር መኖሩን በመገንዘብ ለሁሉም የሚበጅ መፍትሔ ለመፈለግ ዕድል ፈጣሪ ሆኖ ይገኛል” በማለት ተቀራራቢ ሃሳብ ሰንዝርዋል (2011ዓ.ም፡ 18-19)።

የዘውትር ህይወታችን አካል የሆነው ግጭት በአብዛኛው አሉታዊ ጎኑ ገዝፎ ቢታይም በጥሩ ብልሃት ከተያዘ ግን ችግሮችን ለመፍታት አዎንታዊ ገፅታ እንዳለውም ከቀረበው ገለፃ መረዳት ይቻላል። የግጭት አፈታት ጥበብ እና ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው፣ “ግጭትን ለመፍታት የበሰለ ጥበብ እና የላቀ ዕውቀት ያስፈልጋል። በግጭቱ ሂደት በርካቶች እንዳይጎዱ ብሎም ዘለቂ የሆነ ስብራት እና ልዩነት እንዳይፈጠር ጥንቃቄ እና ማስተዋል የተሞላበት ዕርቅን መፈፀም ያስፈልጋል” (ዓለሙ፣ 2009፡91-92)።

የግጭት አፈታት በጥንቃቄ ካልተመራ አንደንዴም በቀላሉ የማያባራ ግጭትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ጥበብ እና ልምድ ባላቸው ሰዎች (ሽምጋዮች) ከተመራ ግን በአዎንታዊ ጎኑ ዘላቂ ሰላምን የሚያስገኝ ይሆናል፡፡ ከዚሁ አንፃር ይህ ጥናት ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ዘላቂ ሰላምን ከማስፈን አኳያ ያለውን ሚና ይመረምራል፡፡

## 3.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዕይታ

***የትዕምርት ፍከራ (Symbolic Interpretation):-*** በትዕምርት መረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ ወቅት በባህሉ መሠረት ለትዕምርቱ የሚሰጠውን ፍቺ (meaning) ከትዕምርቱ ጋር የተያያዙ እሴቶችን ወዘተ. ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ሲሆን ከመስክ የተገኘውን መረጃ ከመግለፅ ባሻገር ጥልቅ ትንታኔ የሚሰጥበት ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ይኸውም የትዕምርቱን ምንነት፣ ዓይነት እና ቅርፅ፣ ትዕምርታዊ ጠቀሜታ እና ሚና፣ ውክልና እና ትርጓሜ፣ ትዕምርቱ ከህብረተሰቡ ህይወት ጋር ያለውን ቁርኝት፣ ያለፈውን እና አሁናዊውን ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል (Geertz, 1993; Turner, 1967; Sims, and Stephens, 2011)፡፡ ጥናቱም የተጠቀሱትን ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ዕይታዎች ለትንታኔ ተጠቅሟል፡፡

## 3.3. የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት

ባህላዊው የግጭት አፈታት ለበርካታ ዓመታት ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው ተዘንግቶ የቆየ የጥናት መስክ ነው፡፡ ውስንነት ነበረበት፡፡ በዚህም ምክንያት የሀገር በቀል ዕውቀት ውጤት የሆነውን መልካም እሴት በሀገር ደረጃ በአግባቡ ለመጠቀምም ሆነ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት ዕውቀቱንም ለማስፋት አልተቻለም፡፡ ይህ ደግሞ በገሃድ እንደታየው ዞሮ ዞሮ ችግር ማስከተሉ የማይቀር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በርካታ ሀገራዊ ክፍተቶች የሚስተዋሉ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተለያዩ ክልሎች እየተሰራባቸው ላሉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ትኩረት በመስጠት መጠናት ጀምረዋል፡፡ ብዙ የሚቀረው ቢሆንም በቃል ደረጃም ቢሆን ከበፊቱ ይልቅ አሁን ለሀገር በቀል እውቀት ትኩረት እየተሰጠ የሚገኝ ይመስላል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተሰሩ ያሉት የግጭት አፈታት ጥናቶች በቁጥርም በዓይነትም በርከት እያሉ ነው፡፡ አኃዙ የሚያስመካ ነው ባይባልም ለዚህ መጣጥፍ (Article) ዝግጅት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኙ ካታሎጎችን በፈተሸንበት ወቅት እንኳ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የተሰሩ ወደ 10 የሚጠጉ የግጭት አፈታት ጥናቶችን አግኝተናል፡፡ እነዚህም ጥናቶች በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የብሔር ብሔረሰቦችን ባህል መሠረት አድርገው የተሰሩ ቢሆንም በአጠቃላይ ይዘታቸው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስልቶች በኅብረተሰቡ ዘንድ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በጥቅሉ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ነገር ግን ርዕሰ ጉዳዩ ካለው ውስንነት አንፃር ሁሉንም ሥራዎች በዚህ ቅኝት ውስጥ በጅምላ ማካተት የማይቻል በመሆኑ የራሳችንን አማራጭ ተጠቅመናል፡፡ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ እና አካባቢ በቀጥታ ለሚጋሩት የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሑፎች ልዩ ትኩረት ሰጥተናል፡፡ እነዚህን ጥናቶች በሁለት ምድብ ከፍለን ነው ያየናቸው፡፡ እነርሱም በመጀመሪያ ደረጃ የዕርቅ ጉዳይን ያጠኑ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የቱለማ ኦሮሞ የከበሩ ንዋያትን በከፊል የተመለከቱ ናቸው፡፡

በመጀመሪያው ምድብ የዕርቅ ጉዳይን የተመለከቱት፡- የሙልጌታ ነጋሣ (1997ዓ.ም)፣ **"የአደአ ሊበን ወረዳ የሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንፃር"** በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ የ Eskedar Girum (2008), **"Traditional Conflict Management Institutions among Aleltu Oromo Community, Northern Shewa"**፤ የ Melaku Abera (2010), **"Land disputes and disputes Settlment mechanisms among the Tulama Oromo of Sululta district, Northern Shewa"** ፤ እንዲሁም የ Dejene Gemechu (2002), **"Conflict and Conflict Resolution among Waliso Oromo of Eastern Mecha: The case of The Guma"** በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ናቸው፡፡ አጥኒዎቹ የግጭት አፈታት ስልትን ከአውድ አንፃር ያቀረቧቸው ጥናቶች ዝርዝር መረጃዎችን የያዙ፤ በእጅጉም ጠቀሚ ናቸው፡፡

የጥናቶቹ ርዕሰ ጉዳይ እንደሚያመለክተው፡- የሙልጌታ ጥናት ዋና ዓለማ የኦሮሞ ሴረጉማ ምንነት እና ከግጭት አፈታት አንፃር በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን (የሚኖረውን) ማህበራዊ ጠቀሜታ፤ የእስከዳር ጥናት ዓላማ በአለልቱ ኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ የሚስተዋለውን የግጭት አይነት እና ባህርያት፣ የባህላዊ የግጭት አፈታት አስተዳደር ተቋማትን ሚና እንዲሁም ግጭቶቹ የሚፈቱበትን አግባብ፤ የመላኩ ጥናት ዋና ዓላማ በሰሜን ሸዋ በሱሉልታ ወረዳ በሚገኘው የቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ከመሬት ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች (ግጭቶች) እና አለመግባባቶቹ (ግጭቶቹ) የሚፈቱበትን ስልት እንዲሁም የግጭት መፍቻ ተቋማትን፤ የደጀኔ ጥናት ደግሞ ስለ ኦሮሞ የፍትህ ሥርዓት፣ "ኢላፍ ኢላሜ/ Ilaaf- Ilaamee" ድርድር (negotiation)፣ ስለ ሽምግልና እና የቃሉ ችሎት እንዲሁም በወሊሶ ኦሮሞ የሚከናወነውን የጉማ ሥርዓት እና ከበራ በመተንተን ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡

እነዚህ ጥናቶች እና አጥኚዎች ስለ "ቦኩ፣ ከለቻ እና ጫጩ" በዐረፍተ ነገር ደረጃ ገልፀዋል፡፡ የኛ ጥናት ግን በዋናነት ለዕርቅ መቋጫነት የሚውሉ የከበሩ ንዋያትን ዓይነት፣ አሰራር፣ ሚና፣ አጠቃቀም እና ትዕምርታዊ ፍቺ የሚተነተን ስለሆነ ልዩነት አለን፡፡ከከበሩ ንዋያት ጋር በተያዘ በተዘዋዋሪ መንገድ ቅርበት ካላቸው መካከል፡- ቀነዓ ለሚ (2010ዓ.ም)፣ **"የኦሮሞ ሚቶሎጂ ይዘታዊ ትንተና"**፤ በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያነት የተሰራው ጥናት ተጠቃሽ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ "በኦሮሞ ሚቶሎጂ ይዘት ላይ ማህበራዊ ትንተና በማድረግ በኦሮሞ ኅብረተሰብ ባህል ውስጥ ሚቶሎጂ የሚወጣቸውን ተግባራት ማመልከት ነው" (22)፡፡

በዚሁ መሠረት የመግለፅ ተግባር ያላቸውን የአፈጣጠር እና የአመሰራረት ሚቶችን፣ በዕለታት እና ስነከዋክብት ጥምረት ላይ የተመሰረቱ ሚቶችን፣ የእሬቻ፣ የቦኩ እና የከበራ ሚቶቸን በጥናቱ ተንትኗል፡፡ የአጥኚው ትኩረት ሚት እና ሚቶሎጂ ነው፡፡ የኛ ትኩረት ደግሞ የአፈጣጠር ሚት ሳይሆን የከበሩ ንዋያት ትዕምርታዊ ፍቺ ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ቀነዓ የአባ ቦኩ የሥልጣን ምልክት የሆነውን "ቦኩ - በትረ ሥልጣን" አልተነተነም፡፡

ከዕርቅ እና ከግጭት አፈታት አንፃር ያለውንም ሚና አልገለፀም፡፡ በኛ ጥናት ግን ሰው ሰራሽ የሆነውን የዚህን በትረ ሥልጣን አሰራር፣ ከግጭት አፈታት አንፃር የሚኖረውን አጠቃቀም እና አገልግሎት፣ ትውፊታዊ እና ትዕምርታዊ ፍቺ በትንታኔያችን ውስጥ በስፋት አሳይተናል፡፡ በኛ ጥናት ከዕርቅ አንፃር የተተነተኑት ከለቻ፣ ጫጬ፣ ጮሌ ፈረስ፣ ቅል... በቀነዓ ጥናት ውስጥ በቃላት ዝርዝር እንጂ በትንታኔ አልቀረቡም፡፡ በአጥኚው ያልተዳሰሱ ጉዳዮች በኛ ጥናት ውስጥ ከዕርቅ እና ከትዕምርት አንፃር መቅረባቸው የልዩነታችን ማስረጃዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ብሩ ጸጋዬ (2002ዓ.ም)፣ ታቦር ዋሚ (2006 ዓ.ም)፣ ዓለማየሁ ኃይሌ (2000ዓ.ም)፣ ድርቢ ደምሴ/ Dirribii Damussee (2016) በአማርኛ እና በአፋን ኦሮሞ በተለያዩ ጊዜያት ባሳተሟቸው መጻሐፍት ስለተጠቀሱት የከበሩ ንዋያት የተወሰኑ ነጥቦችን ጠቃቅሰዋል፡፡ ገለፃቸው በኛ ጥናት በቀረበው ልክ የከበሩ ንዋያቱን አሰራር፣ ትዕምርታዊ እና ትውፊታዊ ሚና የሚያሳዩ አይደሉም፡፡ የኛ ጥናት በተዘረዘሩት መጻሕፍት ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ እና አዳዲስ ሃሳቦችን የያዘ በመሆኑ የተለየ ነው፡፡ ይኸውም ልዩነት ከመጻሕፍቱ ጥቅል እና አጫጭር ገለፃ በተሻለ ከመስክ በተገኙ መረጃዎች ማለትም በቃለመጠይቅ፣ በምስል እና በልዩ ልዩ ማጣቀሻዎች ተደግፎ በጉልህ ታይቷል፡፡ ይህ የኛ ጥናት የግጭት አፈታት ስልቶቹ ከቱለማ የከበሩ ንዋያት (Ulfaalee) ጋር ያላቸውን ጥብቅ ቁርኝት፣ ባህላዊ እና ትውፊታዊ ጉዳዮችን በተሻለ ሁኔታ በማሳየቱ እንዲሁም ከፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ አስተሳሰቦች ጀምሮ የራሱን አካሄድ የሚከተል ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን በተዛማጅ ጥናት ውስጥ የተቃኙት ስራዎች ለጥናታችን ሃሳብ ማዳበሪያ እና ማጎልበቻ ጥሩ መሠረት ሆነዋል፡፡

## 4. የቱለማ ኦሮሞ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስልት ትንተና

በክለሳ ድርሳናት እንደተገለፀው ግጭት በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ በማናቸውም የግንኙነት መስተጋብር ውስጥ ይከሰታል፣ “ግጭት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ፣ በሀገር ደረጃ፣ በክልል ደረጃ፣ በመንግሥት መካከል፣ በቤተሰብ፣ በጎረቤታሞች፣ በፍቅረኛሞች መካከል፣ በድርጅቶች፣ በእምነት ተቋማት ውስጥ፣ በግለሰቦች እንዲሁም በራሳችን ውስጥም ሳይቀር ሊከሰትና ሊታይ ይችላል” (ዓለሙ፣ 2009፡ 34)፡፡ እንደ ጸሐፊው ገልፃ፣ ግለሰቦች ከፍተኛ ሥፍራ የሚሰጧቸው እና የሕይወታችን ዋነኛ ነገሮች ናቸው ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች በቡድን ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ ዋጋ አጥተው ሲመለከቱ በውስጣቸው የሚፈጠረው ንዴት፣ ቅሬታ እና ቁጭት ውሎ አድሮ ለሚገነፍል ግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡ እነዚህ የግጭት መንስኤዎች ዓለም ዓቀፋዊ ባህሪ ስላላቸው የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነውን የቱለማ ኦሮሞ ጨምሮ ሁሉንም ወገን የሚመለከቱ ቢሆኑም ከባህል ባህል፣ ከቦታ ቦታ ተሳቢ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች እንዳሉም ሊታወቅ ይገባል፡፡ ለዚህም የህዝቡ ህይወት የተመሠረተበትን ማህበረ ኢኮኖሚ ማስተዋል ተገቢ ይሆናል፡፡ ሙልጌታ (1997 ዓ.ም) በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት ዓባይነት የግጭት ዓይነቶች ከኢኮኖሚ፣ ከባህላዊ እሴቶች፣ ከሞራል፣ ከኃይማኖት፣ ከዘመኑ የፖለቲካ መንፈስ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የቱለማ ኦሮሞ ህይወት በይበልጥ በእርሻ፣ በከብት እርባታ እና በጥምር ግብርና ሥራ ላይ የመሠረተ እንደመሆኑ የሚነሱት ግጭቶችም በዚሁ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፣ "ጎረቤት ከጎረቤት ጋር በማሳ ድንበር፣ በግጦሽ መሬት ወዘተ. ላይ ይጋጫል። የይዞታ ባለቤትነት ጥያቄ በማንሳት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እርስበርሳቸው የከረረ ግጭት ይፈጥራሉ (ሙልጌታ፣ 1997 ዓ.ም፡40)። ከኢኮኖሚ ጋር የተያያዙት ግጭቶች መነሻቸው ብዙ ናቸው። የአሰፋፈር (የሰፈራ/ የመኖሪያ) እና የዕርሻ ቦታ፣ በብድር፣ በውርስ፣ በትዳር መካከል በሚፈጠር አለመግባባት በወቅቱ ቀለብ ሰፍሮ አለመስጠት፣ የግል ባህርያት ወዘተ. ለግጭት መንስኤ ሲሆኑ ይስተዋላል። የግጭት ዓይነቶች እና መንስኤዎቻቸው በርካታ ሲሆኑ ግጭት ቅራኔን፣ ጥላቻን፣ አለመግባባትን ወዘተ. ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው (Eskedar, 2008:10)።

የግጭቶቹ ይዘትና ውጤት የተለያየ ገፅታ ቢኖራቸውም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኅብረተሰቡን የሚመለከቱ የግጭት መንስኤዎችን ማወቅ መፍትሔ ለመሻት ግማሽ መንገድ ያህል እንደመጓዝ ይቆጠራል። ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ዋናው ቁምነገር ግን የግጭት መንስኤን ማወቁ ላይ ብቻ ሳይሆን ግጭቱ ሌላ ችግር ሳያስከትል በአጭሩ መቋጨት መቻሉ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር የቱለማ ኦሮሞ በኅብረተሰቡ መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶችን እና ግጭቶችን በምን ዓይነት ስልት ይፈታል? የግጭት መፍቻ የሆኑት የከበሩ ንዋቱስ ምን ዓይነትሚና አላቸው? የሚሉት ጥያቄዎች ተተንትነዋል፤ ተገልፀዋል።

## 4.1. የቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስልቶች

የገዳ ሥርዓት ለግጭት አፈታት ማለትም ለዕርቀ ሰላም የሚሰጠው ዋጋ ከሁሉም የላቀ ነው። ገዳ የዕርቅ እና ሰላም (ዕርቀሰላም) ተምሳሌት ነው። ገዳ አስታራቂ ነው፤ ገዳ ሰላም ነው። በዚህም መሠረት ገዳ ከምንም በፊት ለእርቅና ሰላም ቅድሚያ ይሰጣል::

> *በመጀመሪያ ደረጃ የገዳ ሥርዓት ማለት በራሱ ዕርቅ ነው። ምናልባትም ሰው በተለያየ ምክንያት ሊጋጭ ይችላል። ወደ ገዳ ሥርዓት ሲመጣ ግን ሁሉም ሰው ወሰኑን ያውቃል። የአንዱ ሥራ ከሌላው ጋር አይጋጭም፤ ሁሉም ድርሻውን ያውቃል። ድርሻውን (ወሰኑን) ስለሚያውቅ ካጠፋ ቶሎ ይተዋል ማለት ነው። ሥርዓቱ ነው የሚወስነው። ለዚህም ሲባል የገዳ ሥርዓት በራሱ ዕርቅ ነው። ዕርቅ ባለበት ደግሞ እርስ በርስ መጋጨት የለም። ለዚህም ሲባል የገዳ ሥርዓት፣ ዕርቅና ሰላም ተነጣጥለው አይታዩም። አጥንትና መቅኒ ናቸው (አቶ ቦቤ ሁሉቃ፣ 05/02/2012 ዓ.ም መቂ - በትርጉም የቀረበ)።*

አጥንት እና መቅኒ አንዱ በሌላው ውስጥ ያሉ ናቸው። በዚህም ሳቢያ ዕርቅ እና ሰላም የማይነጣጠሉ የገዳ ሥርዓት መሠረታዊ የገዳ ሥርዓት እሴቶች ናቸው። ቂም እና በቀልን ትቶ ዕርቅ መስርቶ በሰላም አብሮ መኖርም የገዳ ሥርዓትም ሆነ የዋቄፈና እምነት መገለጫዎች ናቸው፤ መሠረታዊ መርሆዎችም ናቸው። በዚህ ረገድ የኦሮሞ ህዝብ የራሱ የሆኑ ልዩ ልዩ የግጭት አፈታት ስልቶች ያሉት ሲሆን በሌሎች አካባቢዎች እንደሚኖሩት የኦሮሞ ህዝብ ሁሉ የቱለማ ኦሮሞም ሀገር በቀል

እውቀቱን ተጠቅሞ በባህላዊ መንገድ ግጭቶችን ከሚፈታባቸው ስልቶች እና የዕርቅ ማዕዶች ውስጥ፡- ሽምግልና ወይም የሽምግልና ሥርዓት (Jaarsummaa)፣ ሸነቻ፣ ጉማ (የደም ካሣ) ወይም የጉማ ሥርዓት (Sirna Gumaa/ Seera Gumaa) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከቃሉ (Qaalluu[6]/ ቃሊቲ - Qaallittii)፣ አባ ቦኩ (Abbaa Bokkuu) ወይም ሀዩ (Hayuu)፣ የተሰኙት ተቋማት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው (Melaku,2010፡ 68; Eskedar, 2008: 61)፡፡ ሸነቻ (Shanacha)፣ ሰግሊ (Saglii)፣ ቂጤ (Qixxee) በተጓዳኝነት ይታያሉ (Dejene 2002: 70; ሙልገታ 1997 ዓ.ም፡ 41)፡፡

## 4.1.1. ሽምግልና

ሽምግልና በሀገር ሽማግሌ የሚከናወን ነው፡፡ የሀገር ሽማግሌ (Jaarsa biyyaa)፡- የሀገር ሽማግሌ ባለው ማህበራዊ ተቀባይነት የሚመረጥ፣ ዕድሜው ከፍ ያለ፣ ደሞዝ እና ጥቅማጥቀም ሳይከፈለው ባለው ማህበራዊ ኃላፊነት ብቻ ለእውነት እና ለማህበራዊ ፍትህ ባለጉዳዮችን የሚሸመግል (የሚዳኝ)፣ በሁለቱም ተሸምጋዮች ፍላጎት የሚሰየም ሦስተኛ ወገን ሰው ነው፡፡ የሀገር ሽማግሌዎች ምንም እንኳ ዕድሜያቸው ጠና ያሉ ሰዎች ቢሆኑም ወጣትም በሽምጋይነት ከተሳታፈ በባህሉ መሠረት ሽማግሌ ይበላል (Eskedar, 2008:61; Melaku,2010፡68-69)፡፡

የሽምግልና ሥርዓት (Jaarsummaa) ክዋኔው የሚካሄድበት፣ የሽምግልና ጉዳይ የሚታይበት መድረክ፣ ተቋም ወይም ችሎት ሲሆን በአወቃቀር ባህሪው ቋሚ አይደለም፤ በተሸምጋይ ወገኖች ፍላጎት መሠረት  በየጊዜው የሚመረጥ፤ የሚደራጅ ነው (Melaku, 2010፡ 68)፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ግጭትን ለመፍታት ከሚጠቀምባቸው ባህለዊ የግጭት አፈታት ስልቶች መካከል ሽምግልና በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ሽምግልና በተኮራረፉ፣ በተጣሉ እና በልዩ ልዩ ምክንያት ጠብ (አምባጓሮ) ፈጥረው በተጎዳዱ ወይም በተበዳደሉ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሰላም ለማውረድ የሚደረግ የማስታረቅ ሂደት ነው፡፡ በዚሁ ሂደትም በኦሮሞ ባህል እና የገዳ ሥርዓት መሠረት ሽምግልና ለእውነት፣ ለፍትህ፣ ለመቻቻል እና ለሰላም በቆሙ፣ ደሞዝ በማይከፈላቸው እና በበጎ ፈቃደኝነት ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ሽምግሌዎች ይካሄዳል፡፡

በሽምግልና ወቅት የሽማግሌ ሚና ግራና ቀኙን አድምጦ ጥፋተኛውን መለየት ነው፣ *“Jaarsi dhimma dhiyaateef irratti hundaa’ee kanas sanis gaafata. Waldhabdeen isaanii sababiin isaa maali? Waldhabbii saniif ittigaafatamaan eenyu?  eenyutu dhugaa qaba? eenyutu balleessaadha? jedhee gaafatee addabaasa. Sirana Gadaa keesstti dhugaan waan hundaa oli. Wanni dhugaa caalu hinjiru (Obboo Maammoo Gadaa, 08/12/2011 A.L.I Adaamaa)* -

6 ቃሉ (Qaalluu) የኦሮሞ ነባር ባህላዊ እምነት - የ“ዋቄፈና” መሪ ማለት ሲሆን በሌላኛው ስያሜው አባ ሙዳ (Abbaa Muudaa) ይሰኛል፡፡ በቱለማ አፈታሪክ መሠረት የኦሮሞ ቃሉ ጥንት በዋቃ/በአምላክ ፍቃድ ከሰማይ የወረደ ቅዱስ ነው ተብሎ ይታመናል (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ)፡፡ ቃሉ (Qaalluu) ተባዕትነትን፣ ቃሊቲ - (Qaallittii) እንስትነትን ያሳያል (Eskedar, 2008: 61)፡፡

ሽማግሌ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ተመስርቶ ይህንንም ያንንም ይጠይቃል። የጠባቸው ምክንያት ምንድነው? ለተከሰተው አለመግባባት ማነው ተጠያቂው? ማነው እውነት ያለው? ማነው ጥፋተኛ? ብሎ በመጠየቅ ያጣራል። በገዳ ሥርዓት ውስጥ እውነት ከሁሉም ነገር በላይ ነው። እውነትን የሚበልጥ ነገር የለም" (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/ 2011 ዓ.ም አዳማ)።

የሽምግልና ጉዳይ ከተነሳ ሽምጋይ ስለሚሆኑት ሰዎችም (ሽማግሌዎችም) አንዳንድ ነጥቦችን መጠቃቀስ ተገቢ ይሆናል። ጃርሳ (Jaarsa)- ሽምግሌ (አስተራቂ) የሚባሉት ዕድሜያቸው ብዙውን ጊዜ ከ64-72 ዓመት ያሉት አዛውንቶች ናቸው (ሙልጌታ፣ 1997፡ 33)። ይሁንና በቱለማ ገዳ ሥርዓት የዕድሜ እርከን ስሌት መሠረት ከመጀመሪያ ዩባ (Yuubaa 48 - 56) ጀምሮ ሁለተኛው ዩባ (56 - 64) እና ሦስተኛው ደረጃ ዩባ (46-72) አባገዳዎችን ከማማከር ተግባራቸው በተጨማሪም በሽምግልና እና በህዝባዊ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋሉ። ከሦስተኛው ዩባ የዕድሜ እርከን አልፎ ወደ ገዳሞጂ (Gadaamojjii) የዕድሜ ዕርከን የገባ ሰው በእርጅና ምክንያት ነገሮችን የመዘንጋት እና የመርሳት አዝማሚያ እየታየበት ስለሚሄድ ምናልባትም በተፈጥሮ ብርቱ እና ንቁ ካልሆነ በቀር ለሽምግልና ወይም ለአስታራቂነት እንደማይመረጥ ይነገራል። የሽምግሌዎች ቁጥር እንደሁኔታው አመቺነት፣ እንደ ጉዳዩ ስፋት ከሁለት እስከ አምስት ሊደርስ ይችላል። በጎረቤታሞች እና በሰፈር (በመንደር) አካባቢ ለሚፈጠሩ ችግሮች ሁለት ሽማግሌዎች ሊሰየሙ የሚችሉ ሲሆን ሦስት... ሆነው የሚዳኙበት ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓትም በስፋት ይስተዋላል።

የቱለማ ኦሮሞን ባህላዊ ሽምግልና እና የግጭት አፈታት ስልቶች የሚያመሳስሏቸው በርካታ የጋራ የሆኑ ሥርዓታዊ አካሄድ እና አፈፃፀም አላቸው። በይበልጥ ተመሳሳይነትም አላቸው። በኦሮሞ ባህል መሠረት የሚከናወነው ማንኛውም ዓይነት ችሎት ወይም ሽምግልና በምርቃት ይጀመራል። በሁሉም የግጭት አፈታት ስልቶች የሚከናወነው ውይይት እና ዕርቅ በወል መጠሪያቸው "ሽምግልና" ይባላሉ። በተጠቀሱት ምክንያትም የግጭት አፈታት ስልቶቹ ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆን በአተገባበር ረገድ ግን ሙሉ በሙሉ አንድ ናቸው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ባልና ሚስት እንዲሁም ጎረቤታሞችን ለማሸማገል በየሰፈሩ የሚካሄደው የዕርቅ ማዕድ እና የገዳ ሥርዓት ችሎት - "ሸነቻ" ይለያያሉ። በየሰፈሩ የሚከናወነው ሽምግልና ቋሚ ቦታ፣ ቋሚ ቀን እና ቋሚ የሽማግሌዎች አባላት የሉትም። ማንኛውም ዓይነት ጥል እና ጠብ በተፈጠረ ቁጥር ሁኔታው እንደፈቀደ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ፣ በተጣሉ ሰዎች ፍላጎት መሠረት በሚመረጡ አስታራቂዎች የሚከናወን ይሆናል። የገዳ ሥርዓት ባህላዊ ችሎት (Dhaddacha Gadaa) - ሸነቻ ግን ስያሜው እንደሚያመለክተው አምስት ባህላዊ ዳኞች፣ ቋሚ ቦታ እና ቀን አለው፤ በዳኝነት የሚሰየሙ ቋሚ አባላትም አሉት። ለአብነት ያህል በቢሾፍቱ ከተማ እና በአቃቂ ከተማ የሚካሄዱት የገዳ ችሎቶች ሐሙስ ሐሙስ የሚያስችሉ መሆናቸውን በመስክ በነበረን ቆይታ ተመክተናል።[7]

---

7 ለአብነት ፎቶግራፍ ቁጥር 1 በተጨማሪ ማስረጃነት ቀርቧል።

በተመሳሳይ በሸነቻ እና በጉማ ሥርዓት የሚከናወኑት የሽምግልና ሂደቶችም በራሳቸው ሽምግልና ተብለው በወል ቢጠሩም የዕርቅ አካሄዳቸው፣ የሽማግሌዎች እና የሰዎች ብዛት፣ የሥርዓተ ከበራው ዓይነት እና የከበሩ ንዋያቱ አጠቃቀም ጭምር ልዩነት አላቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በትንታኔው ተመልክቷል፡፡

## 4.1.2. ሸነቻ

"ሸነቻ[8] - Shanacha" የሚለው የአፋን ኦሮሞ ቃል አምስት አባላት ያሉትን እና በገዳ ሥርዓት ችሎት ላይ የሚሰየሙ የሽማግሌዎችን ወይም የአስታራቂዎችን ስብስብ የሚመለከት ነው፡፡ "ሸን" በአፋን ኦሮሞ አምስት ማለት ሲሆን የአስታራቂዎቹን ብዛት እና ስያሜ የሚወክል ነው፣ "ለሽምግልና (ለዕርቀሰላም) የሚመረጡ ሽማግሌዎች ቁጥር አምስት በመሆኑ "ሸነቻ" በማለት ይሰይማሉ (ዓለማየሁ፣ 2000፡ 239)፡፡ በዚሁ አግባብ በገዳ ሥርዓት ውስጥ በሸነቻ ወይም በገዳ ችሎት ላይ ዋናውን አባ ገዳ[9] (Abbaa Gadaa) ጨምሮ አባ ሴራ[10] (Abbaa Seeraa)፣ አባ አለንጋ[11] (Abbaa Alangaa) ፍርድ እና ውሳኔ በመስጠት የዳኝነት እና የፍትህ ሥራ ያከናውናሉ፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ የሽምግሌዎች ሚና የቀረበላቸውን ጉዳይ በጥሞና አድምጠው፣ መርምረው በደለኛ (ጥፋተኛ) የተባለውን ሰው መለየት ነው፡፡ ችሎቱም ያለምንም አድሎ በገለልተኛነት እና በነፃነት ይከናወናል፡፡ ለሽምግልና የሚሰየሙት ሽምጋዮችም (የሸነቻ አባላትም) ከየትኛውም ወገን የማይወግኑ፣ አንዱን በተለየ ሁኔታ አቅርበው ሌላውን በታቃራኒው የማያርቁ፣ ለጥቅም ብለው ሳይሆን ለገዳ ሥርዓት እውነተኛ ፍትህ እና እኩልነት በሀቅ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ዋናው ጉዳያቸው በተሽምጋዮች የቀረበው ጭብጥ ምንድነው? የገዳ ሥርዓት ህግ በቀረበው ጉዳይ ላይ ምን ይላል? የሚለው ብቻ ነው፡፡ ባለ ጉዳዩ ሃብታም ይሁን ደሃ፣ ወፍራም ይሁን ቀጭን፣ ወንድ ይሁን ሴት… ሁሉም በገዳ ህግ ፊት እኩል ነው፡፡ አድሎ መፈፀምም ሆነ ፍርድን ማዛባት የከፋ ኃጢያት እንደሆነ ይታመናል፡፡

---

8 "ሸነቻ" ብዙውን ጊዜ በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ አባገዳዎች የሚቋቋም የፍትህ/ የዳኝነት ተቋም ነው፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊባል ይችላል፡፡

9. አባ ገዳ በዘመኑ የገዳ ሥልጣን (ኃላፊነት) ተቀብሎ የገዳ ሥርዓትን እና ህዝብ የሚመራ ሲሆን ከዘመናዊው የመንግሥት አወቃቀር ሲነፃፀር ጠቅላይ ሚኒስትር ተብሎ በአቻነት ሊታይ ይችላል፡፡ ከአባ ሴራ እና ከሌሎች ጋር በመሆን የማህበራዊ ፍትህ ችሎትን በበላይነት ይመራል፤ መላውን ህዝብ ያለምንም አድሎ በእኩል ደረጃ እንዲዳኝ እና ፍርድ እንዳይጓደል፣ ፍትህም እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

10."አባ ሴራ በገዳ ሥርዓት ህግ አስፈፃሚና ህግ አውጭ"(ዓለማየሁ፣ 1998፡ xiii)::

11 አባ አለንጋ ኢ-ፍትሐዊ ውሳኔ ሲወሰን የሚከራከር፣ ለኅብረተሰቡ ጥብቅና የሚቆም፣ ፍትህ እንዲከበር የሚያደርግ - ጠበቃ ወይም ለዚህ ዓይነቱ የፍትህ ሥርዓት የሚቆም አካል ማለትም "አቃቤ ሕግ ተብሎ ስያሜ የወጣለት ከዚህ አለንጋ በመነሳት ነው - Abbaa Alangee jedhamee maqaan kan ba'eef, Alangee kanarraa ka'uudhaani" (Obboo Tufaa Bariisoo, 20/11/2012 A.L.I. Botee). በዘመናዊው አጠራር የፍትህ ሚኒስትር እንደማለት ይሆናል፡፡

በዚሁ አግባብ የአካባቢው ተወላጅም ይሁን ተወላጅ ያልሆነ ማንኛውም ሰው (ዜጋ[12]) ጉዳይ ገጥሞት የገዳ ችሎት ላይ የቀረበ እውነትን ብቻ መሠረት በማድረግ ይዳኛሉ፤ ፍትህንም ያገኛሉ። የፍርድ ሂደቱም ለሙስና ያልተጋለጠ በመሆኑ ሕዝቡ እውነተኛ ፍርድ ለማግኘት ያስችለዋል ተብሎም ይታሰባል። ባህላዊ የኦሮሞ የዳኝነት ሥርዓት የሚያካሄድበት "ችሎት" በአፋን ኦሮሞ "Dhaddacha/ ደ'ደ'ቻ" ይሰኛል። ቃሉም በጥንቱ ዘመን (አሁንም በተወሰኑ ቦታዎች) የዳኝነቱ ስነስርዓት የሚካሄድበትን "ደ'ደ'ቻ - አጣጥ" የዛፍ ዓይነት የሚወክል ሲሆን፣ ቃሉ በኦሮሚያ ክልል ለሚከናወነው የዳኝነት ሥርዓት በማገልገል ላይ ይገኛል። በአቃቂ ከተማ አቅራቢያ "Caffee Tumaa/ ጨፌ ቱማ" በተሰኘ የከበራ ሥፍራ በሚገኘው የአጣጥ "Dhaddacha" ዛፍ ስር የሚከናወነውን ችሎት በተከታዩ ፎቶግራፍ ይመለከቷል።




ፎቶ 1. አምስት ሰዎች የሚዳኙት የገዳ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት (ሸነቻ)፤ ጨፌ ቱማ - 05/06/2011ዓ.ም

በገዳ ሥርዓት መሠረት ሁሉም ሰው ከሕግ እና ከእውነት በታች ነው። "እውነት ጉልህ ሥፍራን ይይዛል። በማኅበረሰቡ አስተሳሰብ መሠረት እውነት (Dhugaa) ከማንኛውም ነገር በላይ ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል" (ሙልጌታ፣1997፡ 45)። በዚሁ እውነት እና የህግ የበላይነት ችሎቱን ብሎም ሕዝቡን የሚመራው አባ ገዳ ጭምር ካጠፋ፣ ሰውን ከበደለ… በገዳ ሥርዓት ሕግ ይከሰሳል፤ ይቀጣል። እንደ ማንኛውም ዜጋ የበደለውን ሰው ይክሳል፤ ይቅርታም ይጠይቃል። ገዳ ተጠያቂነትንም ያማከለ ነው። በገዳ ውስጥ ሁሉም ሰው ከሕግ እና ከእውነት በታች ነው የሚለው አገላለፅም የሕግ የበላይነትን ያሳያል። በዚህ መሰሉ የኦሮሞ ባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት እውነት ከሁሉም ነገር በላይ ትልቅ ዋጋ፣ ትልቅ ቦታ አለው። ተከታዩ ሃሳብም ከላይ የተገለፀውን ይበልጥ እውን የሚያደርግ ነው።

12. የገዳ ሥርዓት ችሎት በገዳ ሥርዓት ለሚተዳደረው የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በክልሉ ለሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች እና በተለያዩ ወቅታዊ ምክንያቶች ወደ ክልሉ ወይም ችሎቱ ወደሚካሄድበት ሥፍራ ለመጡ ሰዎች በሙሉ በእኩል ደረጃ የፍትህ አገልግሎት የሚሰጥ ነው።

> *በገዳ አመለካከት ውስጥ ሁሉም ሰው ከእውነት በታች ነው። ኦሮሞ እውነት እግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔርም እውነት ነው ይላል። አንዳንዱ እውነት ከእግዚአብሔር በላይ ነው ይላል። ለምን ቢባል እግዚአብሔር በራሱ በእውነት ስለፀና፣ ዝንፍ በእውነት መንገድ ስለተጓዘ ነው እግዚአብሔር የሆነው (አቶ ማሞ ገዳ፣ 21/01/2012 ዓ.ም አዳማ - በትርጉም የቀረበ)።*

ይህም ማለት ዋቃ/ እግዚአብሔር ከእውነተኛነቱ እና ቀጥተኛነቱ አጋድሎ በአንድ ቦታ (አጠገብ ለአጠገብ) ላሉ ሰዎች ለአንዱ ፀሐይ ሰጥቶ ሌላውን ቢነሳ፣ ለአንዱ ዝናብ ሰጥቶ ሌላውን ቢከለክል፣ ለሁሉም እኩሉ ባይሆን፣ ቢያዳላ... ኖሮ የእውነት አምላክነቱና የእውነት ተምሳሌትነቱ ከጥያቄ ውስጥ ይገባ ነበር። የእውነትን መስመር፣ የራሱን የተፈጥሮ ህግ ተከትሎ ስለሚጓዝ ግን የእውነት አምላክ ሊሆን ችሏል። በዚሁ አግባብ በገዳ ሥርዓት የሚተዳደረው ኅብረተሰብም በገዳ ሥርዓት አመለካከት መሠረት እውነትን ከሁሉ ነገር በፊት ማስቀደም ይጠበቅበታል። የሰው ልጅ የራሱን ጥቅም ከእውነት ካስቀደመ፣ እውነትንም ከጠመዘዘ ከእውነት ጋር ይለያያል፤ ከእውነት የተለያየ ሰው ደግሞ መንፈሳዊነት ይርቀዋል፤ መንፈሳዊነት የራቀው ሰው ደግሞ ዋቃ የራቀው፣ ጥላ ቢስ፣ ሞገስ የሌለው እና ዝም ብሎ የሚንቀሳቀስ ግዑዝ ሰው ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። በጥናቱ ትንታኔ እንደታየውም ለእውነት ልዩ ግምት የሚሰጠው ለዚሁ ይመስላል። በተገለፀው መሠረት በገዳ ችሎት ትልቁ ነገር እውነትን ፈልጎ ማግኘት ነው፤ ከሳሽም ለእውነት ነው የሚፋለመው፣ ተከራክሮ ከረታም፣ *"Dhugaan naa galte/ Dhugaa tiyya argadhe* (እውነቴ ተመለሰችልኝ፤ እውነቴን አገኘሁ" ወይም ጉዳዩ ከንብረትና ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ "Haqa kiyya argadhe/ *ሀቄን አገኘሁ*" ብሎ ይረካል እንጂ፣ በተከሳሹ ላይ ለተፈረደው ፍርድ ወይም ለተጣለው ቅጣት አይደለም ልዩ ትኩረት የሚሰጠው። ስለሆነም በገዳ ችሎት እውነት ልዩ ቦታ አላት። እውነትን ማጠፍ ወይም ማጣመም ህግን፣ ፍርድንና ፍትህን ማዛባት፣ አድሎና ሙስና መፈፀምም የከፋ ኃጥያት ነው፤ የከፋ ነውር ነው። በኦሮሞ ባህል "ኃጥያት እስከ ሰባት ቤት (ትውልድ) ድረስ ይሄዳል - *Cubbuun abba torba deemti"* ይባላል። በችሎት ወቅት እውነትን መካድ፣ በእውሸት መፍረድና በእውሸት ማስፈረድም በራሱ ኃጥያት ነው። ይህም ኃጥያት ከሦስት አካላት ወይም ሰዎች ጋር ወደ ቤት ይገባል/ ይመለሳል ይባላል::

> *ኃጥያት ከሦስት ሰዎች ጋር ወደ ቤት ይገባል ማለት፣ ሰውዬው የፈፀመው ኃጥያት/ክህደት አብሮት ወደ ቤት ይመለሳል ማለት ነው። አንድ ሰው ጥፋት ፈፅሞ አላምን ካለ ወይም ውሳኔ ይወሰንብኛል ብሎ አንዱን ወገን አምኖ አንዱን ወገን ካላመነ(ከካደ) ትንሽ እንኳ እውነታውን ካጣመመ ኃጥያት ወስዶ ይገባል። አልያም ደግሞ ተበዳይ የሆነው ሰው ያልሆነውን ነገር ጨምሮ ይህን በድሎኛል ብሎ ክስ ካቀረበ እርሱም ኃጥያት ወስዶ ይገባል። ወይም ደግሞ የተበደለው ሰው በአግባቡ ክሱን አቅርቦ፣ በዳዩም ሰው በአግባቡ አምኖ ጉዳዩን የተመለከቱ ሽማግሌዎች (የችሎቱ አባላት) ለአንደኛው ሰው አድልቶ አንደኛውን ሊጎዱ ይችሉ ይሆናል። ስለዚህ ኃጥያት ከነርሱ ጋር ይገባል። እንዲህም ስለሆነ ኃጥያት ከሦስት ሰዎች (ከሦስት አካላት) ጋር ወደ ቤት ይመለሳል ይባላል (አቶ አዱኛ ሙሊሣ፣ 10/05/2010 ዓ.ም ቢሾፍቱ - በትርጉም የቀረበ)።*

ይህም ሃሳብ በአጭሩ ሲገለፅ፣ ያልተፈፀመውን ተፈፀመ ብሎ በእውሸት ክስ ካቀረበው ተበዳይ ወይም የቀረበበትን ክስ በእውሸት ከካደው በዳይ ወይም የቀረበለትን እውነት ሆን ብሎ አውቆ በማዛባት እውነተኛ ፍርድን ካጓደለው ችሎት ጋር ኃጥያት ወደ ቤት ይመለሳል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ኃጥያት ለመዳን ሦስቱም አካላት አንደበታቸውን ከእውሸት ይጠብቃሉ፤ ለእውነትና ለሀቅም ይቆማሉ፡፡ ህዝቡ ወደ አባ ገዳ፣ አባ ቦኩ፣ የሽምግልና እና ሸነቻ ችሎት የሚሄድበት ዋናው ምክንያትም እውነትን ፍለጋ ነው፡፡ በዘመናዊው ፍርድ ቤት ምንም እንኳ መስቀልኛ ጥያቄዎች ቢኖሩም በዚህ ዘዴ ወንጀሉ ካልተደረሰበት መረጃና ማስረጃ የሌለው ክስ ብዙም ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፡፡ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለ መረጃና ማስረጃ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ደግሞ ሊኖሩ እንደሚችሉ እሙን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ሰውን ገድሎ ገዳዩ ተጨባጭ ማስረጃ ካልተገኘበት ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊክድ ይችላል፤ አባ ገዳ ፊት ቀርቦ ግን እውነትን እንደማይክድ ይነገራል፡፡ ምክንያቱም ተፈጥሯዊ እና ማህበራዊ/ ግብረ ገባዊ ደንብ የሆነውን - “ሰፉ/Safuu” ይፈራል፡፡ ይህንንም አልፎ የሚክድ ከሆነ መኃላ ይጠብቀዋል፤ በእውነት ፊት በዳዩን የሚያስጨንቀው የህሊና ፍርድ ነው፡፡ ስለሆነም ህሊናውን ዋሽቶ በከንቱ መማል ያስፈራዋል፡፡ በወንጀል የተጠረጠረው ሰው ወንጀል ወይም ክህደት ፈፅሞ አልፈፀምኩም ካለም አመድ፣ እህል፣ ጥይት፣ ጦር… ይዞ እንዲምል ይደረጋል፡፡

በነዚህ ነገሮች ለምሳሌ “እህል ያሳጣኝ፣ ዘር ያሳጣኝ!” ብሎ የሚምል ሰው ከቶውኑ የለም፡፡ በዚህም ሳቢያ እውነትን ያወጣል፡፡ ገዳ እስር ቤት ስለሌለውም ወንጀለኛው በሐሰት ከሚምል ይልቅ ቶሎ ብሎ ያምናል፤ እውነቱንም ያወጣል፣ “በፍርድ ቤት ሂደት ግን እስር፣ የገንዘብ እና እስከ ሞት የሚያደርስ ቅጣት ስለሚኖር ክህደት ሊኖር ይችላል፡፡ በገዳ ሥርዓት የሞት ቅጣት ስለሌለም በድብቅ የጠፋ ነብስ እንኳ ገሃድ ይወጣል (የቀድሞ አባ ገዳ በየነ ሰንበቶ፣ 11/12/2011 ዓ.ም ቢሾፍቱ - በትርጉም የቀረበ)፡፡

በኦሮሞ ባህል ለእውነት ልዩ ትኩረት የሚሰጠውም ለዚሁ መሰል ችግር መፍትሔ እንዲሆን ታስቦ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ የሽማግሌዎቹ ሚና ምንም እንኳ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች… መካከል የተከሰተውን ግጭት ማርገብ፣ በዳይ እና ተበዳይን ማስታረቅ ቢሆንም ከምንም በላይ ለእውነት የሚቆሙ፤ እውነትንም መርምረው በማውጣት እውነተኛ የሆነ ፍርድ እና ፍትህ[13] የሚሰጡ በመሆናቸው በሕብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ተአማኒነት አላቸው፡፡ ርቱዕ በሆነው እውነተኛ አካሄድም በዳይ እና ተበዳይ የሚታወቅ ሲሆን በዚህ አግባብ የመጨረሻው የሽማግሌዎች ውሳኔ እና የፍርድ ቃል ይከበራል፡፡ በመጨረሻም ሁለቱ ሰዎች (በዳይ እና ተበዳይ) ይቅር በመባባል፣ በዳይ ተበዳይን ለመካስ ቃል በመግባት፣ የሰላምታ እና የዕርቅ ምልክት የሆነውን እሬቻ (ለምለም ሣር) በመለዋወጥ[14] በችሎቱ ፊት ይታረቃሉ፡፡

---

13 ሽማግሌዎች ሆን ብለው እውነትን፣ ፍርድን እና ፍትህን የሚያዛቡ ከሆነ አባ ገዳውን ጨምሮ በገዳ ህግ የሚጠየቁበት አሰራር አለ፡፡ ይህም መሰሉ ተጠያቂነት በህዝቡ ዘንድ ተአማኒነት ለመፍጠር ይረዳል፡፡
14 በዚህ አይነቱ ባህላዊ ትውፊት የተከናወነውን ዕርቅ በፎቶግራፍ ቁጥር 5 ይመለከቷል፡፡

ሰግጭት መንስኤ የሆነው ችግር በሰላም ይቋጫል፡፡ ከዚህ ዕለት ጀምሮ በጠላትነት መተያያት ለቂም በቀል መፈላለግ አይኖርም፡፡ የኩርፊያ እና የጥላቻ አስተሳሰብ በዕርቅ ተሽሮ ሰላማዊ ህይወት ይቀጥላል፡፡ ምናልባት የተሰጠው ፍርድ ሚዛናዊ እና አሳማኝ ካልሆነ፣ ወንጀሉም የተወሳሰበ እና ከግድያ ጋር የተያያዘ ከሆነ ግን ፍትህ ተጓድሎብኛል የሚለው ተበዳይ ወገን ጉዳዩን ወደ ሰግሊ (Saglii) ሊወስድ ይቻላል፡፡

### 4.1.3. ሰግሊ (Saglii)

በየስምንት ዓመቱ የሚዋቀር የሥራ አስፈፃሚ አካላት ሰግሊ (Saglii) ይሰኛል፡፡ በቱለማ ገዳ ሥርዓት መሠረት አጠቃላዩን ገዳ እና ህዝቡን የሚመሩ፣ የአፋን ኦሮሞው ቃል እንደሚያመለክተው ዘጠኝ አባላት ያሉት የገዳ ካቤኔ' ሲሆን በየአካባቢው የሚዳኙ ባለጉዳዮች ቅሬታ ካላቸው፣ ፍትህ ተጓድሎብናል ካሉ ጉዳያቸውን የሚያቀርቡበት እና ትላልቅ ጉዳዮችን መርምሮ ፍርድ የሚሰጥ የገዳ ጠቅላይ ችሎት ነው (አባ ጨፌ ሁንዴ በየነ፣ 6/01/2012 ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡ በተግባሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ሰበር ችሎት ሊባል ይችላል፡፡ ከችሎቱ ያለፈ ጉዳይ ሲያጋጥም ግን ልክ እንደ ሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር ጉዳዩ ለአባ ቦኩ ይተላለፋል፡፡

### 4.1.4. አባ ቦኩ

አባ ቦኩ (Abbaa Bokkuu) ወይም ሀዩ (Hayuu)፡- በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰብ አባላት ወይም የጎሣ በኩር (አንጋፋ፤ ታላቅ) ነው፡፡ የሁሉ የበላይ ነው፡፡ ገዳ (የገዳ ችሎት ወይም ሥራ አስፈፃሚ) ሊፈታው ያልቻለው ብርቱ ጉዳይ አባ ቦኩ ዘንድ ይሄዳል፡፡ በዚሁ መሠረት የመጨረሻው የሥልጣን አካል ነው (አባ ጨፌ ሁንዴ በየነ፣ 6/01/2012 ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡ ልክ እንደ ርዕሰ ብሔር/ ፕሬዝዳንት ይታያል፡፡[15] በእርቅ ወይም በሽምግልና ወቅት አባ ቦኩው (ፕሬዝዳንቱ) የቀረበለትን ጉዳይ በችሎቱ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ ያስተላልፋል፡፡

### 4.1.5. ቂጤ (Qixxee)

የቃሉ ትርጓሜ እንደሚያመለክተው አማካይ/ አጋማሽ ቦታ ማለት ነው (Melaku 2010)፡፡ የአንድ ጎሣ ወይም የህብረተሰብ አካላት ለሁሉም አጋማሽ/ አማካይ በሆነ ቦታ ተገናኝተው የሚወያዩበት፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን ችግር እና ግጭት የሚፈቱበት፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ሰላም፣ ሀገራዊ እና ቤተዘመዳዊ ጉዳዮችን የሚያከናውኑበት እና የመተያያ ድግስ ደግሰው የሚጠያየቁበት ማዕከላዊ ሥፍራ ነው (አቶ በቀለ ቢፍቱ፣ 03/10/2010 ዓ.ም ደ'ከ ኮራ)፡፡ ቁጥራቸው በርከት ያለ ቢሆንም የቤተዘመድ ሸንጎ ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ቤተዘመዳዊ መድረክ የሚተላለፈው ውሳኔም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

15 ተጨማሪ ገለፃ "ቦኩ" በተሰኘው ንዑስ ርዕስ ውስጥ ቀርቧል፡፡

## 4.1.6. ጉማ

“ጉማ[16] - Gumaa” በሁለት ሰዎች… መካከል በተፈጸመ ግድያ መነሻነት የገዳይ የቅርብ ዘመዶች (ጎሣ) ለሟች ወገን (ጎሣ) የሚከፍሉት የደም ካሳ ወይም የነፍስ ዋጋ ነው፡፡ ቃሉም ከገዳ ሥርዓት ሴራ (ሕግ ሥርዓት) ጋር የተሰናሰለ ሲሆን፤ በጥምረት ሴራ ጉማ ይሰኛል፡፡ በጉማ ህግ መሠረት የደም ካሳ የሚከፈለው በዋናነት ለሰው ልጅ ቢሆንም ከቤት እንስሳት መካከልም ለፈረስ፣ ለድመት፣ ለውሻ… የህይወት ካሣ የሚከፈል ሲሆን ይህም ዓይነቱ ካሣ ብዙውን ጊዜ ከሥርየት ጋር የተያያዘ ነው (ሙልጌታ፣ 1997፡ 66፤ ዓለማየሁ፣ 2000፡ 226)፡፡

“ሴረጉማ የሚለው ቃል “ሴራ” እና “ጉማ” በተሰኙት የኦሮምኛ ቃላት የተገነባ ነው፡፡ ሴራ (Seera/ ሴረ)[17] ሲባል ደንብ፣ ሥርዓት፣ የአሰራር ዘዴ የሚሉትን ይይዛል፡፡ “ጉማ” የሚለው ደግሞ “የደም ካሣ” ከሚለው የአማርኛ ቃላዊ ሐረግ ጋር ይቀራረባል፡፡ ስለዚህ ሴረጉማ የደም ካሳ ሥርዓት የሚለውን የአማርኛ ትርጉም ሊይዝ ይችላል (ሙሉጌታ፣ 1997፡1)፡፡

በኦሮሞ ባህልና በገዳ ህግ መሠረት ጉማ የሚከፈለውም ጉማ የሚቀበለውም ጉሣው ነው፡፡ የዕርቅ ስነስርዓቱ እራሱን የቻለ ሂደት ያለው ሲሆን በከለቻና ጫጬ የሚካሄደው ይህ ዓይነቱ ሀገር በቀል የግጭት አፈታትም ዘላቂ ስላምን ለማስፈን የማይተካ ሚና ይኖረዋል (አቶ ተሬቻ ሆርዶፋ፣ 23/01/2012 ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡ የጉማ ሥርዓት በኦሮሞ ባህል እና በገዳ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሲሆን በገዳይ እና በሟች ቤተሰብ የሚፈታ፣ ማህበራዊ ሕይወት እንዳይናጋ፣ ሰዎች ያለ በቀል እና  ደም መፋሰስ ነፃ ሆነው በሰላም እንዲኖሩ የሚያደርግ የግጭት መቋጫ ስልት ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ሆን ብሎ አውቆም ሆነ ሳያስበው በድንገት ሰው ከገደለ በመጀመሪያ  ዋታ[18]  ከተባለ ማህበረሰብ ካንዱ ሰው ቤት ይገባል፡፡ ዋታ ቤት ከገባ ማንም ተከትሎ አይነካውም፤ ማንም ለበቀል እና ለግድያም አይፈልገውም፡፡ ይህ ማህበራዊ ደንብ (Safuu) ነው፡፡ ዋታ ፀጉሩን ላጭቶ ለጥቂት ቀናት ከቤቱ ያቆየዋል፡፡ የጉማ ዕርቅ ስነስርዓት እስኪከናወን ድረስ ገዳይ ከሕብረተሰቡ ጋር አይቀላቀልም፡፡ ከሰው ጋርም አይበላም፤ አይጠጣም እጁ ላይ ደም (ግፍ/ በደል) ስላለ ማንም ሰው እጁን አይጨብጥም፡፡ ወንጀለኛ መሆኑ እስኪሰማው እና የፈጸመው ድርጊትም አስነዋሪ መሆኑን እስኪገነዘብ፣ በቀጣይም ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት እንዲታረም ከፍተኛ የሆነ ስነልቦናዊ ጫና ይፈጥርበታል የሚል አረዳድ አለ፡፡

---

16 ጉማ ሙዳ ሥጋን ይመለከታል፡፡ ጉማ የሚለው ቃል ከጊዜ በኋላ እያደገ መጥቶ እንደ ተቋም ቢታይም ከመነሻው ግን በገዳይ እና በሟች ወገኖች መካከል ዕርቀ ሰላም በሚርድበት ቀን ከሚታረደው በሬ ሥጋ ለእድምተኞች እንዲዳረስ በትናንሹ ተቆራርጦ የሚከፋፈል ሥጋ ነው፡፡ ጉማ/ ትንሽ ቁርጥ ሥጋ መብላታቸውን ለመግለፅ የተጠቀሙበት ነው  (ዓለማየሁ፣ 2000፡ 226)፡፡ በአሁናዊ አገላለፁ ግን አጠቃላይ ሥርዓቱን  እና ክዋኔውን ጭምር የሚገልፅ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

17 ከአፃፃፍ አንፃር ካልሆነ በቀር የአፋን ኦሮሞው ሴራ (Seera/ሴረ) እና የአማርኛው ሴራ ልዩነት እንዳላቸው ልብ ይሏል፡፡ በአፋን ኦሮሞ ሴራ (Seera/ ሴረ) ሲባል ህግ፣ ደንብ፣ ህገ ሥርዓት… ማለት ሲሆን የአማርኛው ሴራ፣ “አድማ፣ ዱለታ” የሚል ፍቺ አለው (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ 1993፡ 122)፡፡

18. ዋታ በምሥራቅ ሸዋ… ዞን የሚኖር የማኅበረሰብ መጠሪያ ሲሆን የሰው ህይወት በእጁ የጠፋ ሰው ከማህበረሰቡ አባል ቤት በመግባት መጠለል በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ በተለይም በጂሌ አካባቢ የተለመደ  ነው፡፡

በዚህም ሳቢያ ገዳይ ባጠፋው ጥፋት እንዲፀፀት እና ተመሳሳይ ስህተትም ዳግም እንዳይፈፅም በተግባር አእምሮው ላይ የሚሰራ ግብረገባዊ የባህሪ ማረሚያ ሥርዓት እንደሆነም ይታሰባል፡፡ የጉማ ዕርቅ ስነስርዓት እንዲጀምር ለሽማግሌዎች ይነገርና ሂደቱ ይጀመራል፡፡ ውይይት እና የጉማ ሥርዓት ሂደቱም ይቀጥላል፡፡ በስተመጨረሻ በሚተላለፈው ውሳኔም፣ "የሰው ሕይወት በእጃቸው የጠፋባቸው ወገኖች በጉማ ሕግ ደንብ መሠረት በአስታራቂ ሽማግሌዎች የተቆረጠውን የደም ካሣ ዋጋ ይከፍላሉ፡፡ የሚከፈለው ካሣ የጠፋውን የሰው ሕይወት ዋጋ ይመጥናል ለማለት ሳይሆን ለተሰራው ጥፋት ኃጢያት የማስተሰሪያ እና ዕርቅ ማውረጃ ዋጋ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው" (ዓለማየሁ፣ 2000ዓ.ም፡ 226)፡፡

በዘመናዊው ቢሮክራሲ አሰራር አንድ ሰው ሌላ ሰውን ከገደለ ሊታሰር ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ግን በብዙ መልኩ መፍትሔ ሳይሆን ተደራራቢ ችግሮችን ሲያስከትል ይስተዋላል፡፡ ግለሰቡ በሚታሰርበት ወቅት መደበኛ ስራው ይቋርጣል፣ የቤተሰቡ መተዳደሪያ ገቢ ይቀንሳል፣ ቤተሰቡ ለችግር ይዳረጋል፣ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ይጎዳል፤ በዚሁ ችግር ምክንያት ትዳሩ ሊፈርስ ልጆቹም ሊበተኑ ይችላሉ፡፡ የቤተሰቡ መሠረት ይናጋል፤ ቤተሰብ ይፈርሳል፡፡ ይህም ሁኔታ በገጠርም ሆነ በከተማ ነዋሪዎች ዘንድ የሚያስከትለው ስነልቦናዊና ማህበራዊ ቀውስ የትየለሌ ነው፡፡ ብዙ ነው፤ ተደራራቢም ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ታራሚው ከእስር ቤት ሲወጣ በሌሎች አካባቢ እንደሚታየው ተጨማሪ የነፍስ ግድያ ሊከሰት ይችላል፡፡ ለብዙ ሰዎች ሞት ምክንያት የሚሆን ተከታታይነት ያለው መበቃቀል ይፈጠራል፡፡ ታራሚውም  በመታሰሩ ምክንያት ላይታረም፣ ከጥፋቱ ላይመለስና ከእስር ከተፈታ በኋላም ተመሳሳይ ጥፋት ሊፈፅም ይችላል፣

> *ሰውን የገደለ ሰው እስር ቤት ከርሞ ከወጣ የሟች ወንድም በበነጋው በጥይት ሊገድለው ይችላል፡፡ መታሰሩ ምናልባትም ሊያርመው ይችላል፤ ነገር ግን ዕርቅ አያወርድም፡፡ የገዳ ሥርዓት ያርመዋልም ዕርቅም ያወርዳል፡፡ ሰውን መግደል የከፋ እንደሆነ ለራሱ እየተማረ ይሄዳል፡፡ ወደዚያ ድርጊት አይመለስም፡፡ አንዴ የተከሰተውን ጥፋት መመለስ አይቻልም፤ የሞተን ሰው መመለስም አይቻልም፡፡ የተፈጠረው ጥፋት ዳግም እንዳይፈጠር የሚያስተምሩበት መንገድ ነው ወሳኙ ነገር፡፡ የገዳ ህግ ያን ድርጊት (ስህተት) ዳግም እንዳትፈፅም አእምሮህን ያሳምናል (አቶ ተሬቻ ሆርዶፋ፣ 23/01/2012 ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡*

በመረጃ አቀባዩ አስተያየት መሠረት የገዳ ሥርዓት አካሄድ በግለሰቡ አእምሮ ላይ አዎንታዊ ሚና በመፍጠር ተመራጭ ነው፡፡ የጉማ የእርቅ ሂደትም በከለቻና ጫጨ ታግዞ እርቅ የሚያወርድ በመሆኑ መበቃቀልንም ሆነ ግጭትን የሚያስወግድ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ባህላዊው ዋናው ዓላማ ዕርቅ ማውረዱ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የሚተላለፈው ውሳኔ ሁሉ በጉማ ህግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ይህም የጉማ ሥርዓት ባህላዊ የዕርቅ ስነስርዓት የሕዝቡን ባህል እና ትውፊት ታሳቢ በማድረግ የሚካሄድ በመሆኑ የህዝቡን ሰላም የሚያስጠብቅ እና የተረጋጋ ሕይወቱን (ኑሮውን) እንዲቀጥል የሚያስችል ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሀገር በቀል የሆነው የግጭት አፈታት ስልት ለሕብረተሰቡ ሰላም እና ደህንነት ትልቅ ዋጋ እንዳለው መገመት ይቻላል፡፡

በባህላዊው ሽምግልና፣ ሽነቻም ሆነ በጉማ ሥርዓት የታረቁ ሰዎች ዳግም ለቂም በቀል ወይም ለግድያ አይፈላለጉም። የጥላቻን ስሜትም አይገላለፁም። ከዚህ በተቃራኒ አንድ ቦታ ውለው የሚያድሩበትን ቤተሰባዊ ፍቅር እና ማህበራዊ ሕይወት ይመሰርታሉ። በአንድ ገበያ አንዱ ለሌላው ሸጦ፣ አንዱ ከሌላው ገዝቶ - ሸምተው እና ነግደው፣ አብረው ሄደው አብረው ይመለሳሉ፣ በሠርግ እና ደስታ፣ በለቅሶ እና በሐዘን አብረው ይሆናሉ፣ በመካከላቸው የተፈጠረውንም ጠብ፣ ቁርሾ እና ግድያ ፍፁም በሆነ መልኩ ረስተው በጋብቻ ይጣመራሉ፤ ተዋልደውም በደም እና በሥጋ ይቀላቀላሉ፤ ይዛመዳሉ፤ ይዋሃዳሉ። አንድ ይሆናሉ። ይህም ሂደት ግጭት በሰላማዊ መንገድ እንዲቋጭ የሚያስችል የጉማ ሥርዓት ምልካም ገፅታ ነው።

## 4.2. ለዕርቅ መቋጫነት የሚያገለግሉ የከበሩ ንዋያት

በቱለማ ኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስልቶች ውስጥ የከበሩ ንዋያት የላቀ ሚና አላቸው። ህዝቡ እነዚህን የከበሩ ንዋያት የሚጠራበት፣ የሚይዝበት እና የሚጠቀምበት የራሱ ስነምግባር፣ ተፈጥሯዊ እና ማህበራዊ ደንብ አለው። የከበሩ ንዋያቱ ስያሜ እና አጠራርም ከክብር ጋር የተቆራኘ ነው። ይህም አገላለፅ፣ "Jecha hoodaa/ የአክብሮት አጠራር" ይሰኛል። ከዚሁ ክብር ጋር በተያያዘ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት የከበሩ ንዋያት በተናጥል "የከበረ ንዋይ/ Ulfaa"፣ በወል "Ulfaalee/ የከበሩ ንዋያት" ይሰኛሉ።

ኡልፋ (የከበረ ንዋይ) ምን ማለት ነው? *"Ulfaa jechuun, jecha ulfina jedhurraa dhufe. Ulfaa Kan jedhameefis Oromoo biratti waan ulfina qabuufi. Kan Caffeen Tuulamaa ulfaadha jedhee lallabeefitu jira. Bokkuun ulfaadha, Kallachi ulfaadha, Caaccuun ulfaadha… kan caffeen Tuulamaa beekkamtii kenneef jechuudha (Obboo Maammoo Gadaa, 08/12/2011 A.L.I Adaamaa) -* የከበረ ንዋይ ማለት፣ የከበረ ከሚለው ቃል የመጣ ነው። የከበረ የተባለውም በኦሮሞ ዘንድ ክብር ስላለው ነው። የቱለማ ምክር ቤት የከበረ ንዋይ (ክቡር) ነው በማለት አዋጅ ያስነገረለት አለ። ቦኩ ክቡር (የተከበረ) ነው፣ ከለቻ ክቡር ነው፣ ጫጩ ክቡር ነው… የቱለማ ምክር ቤት እውቅና የሰጠው (የሰጣቸው) ማለት ነው" (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ)። በዚህም ምክንያት ዕርቅ እና ዘላቂ ሰላምን ለማውረድ የከበሩ ንዋያቱ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው መረዳት ይችላል::

> *እነዚህ የከበሩ ንዋያት ትልቁ ድርሻቸው እርቅ እና ሰላም ነው። አባ ቦኩ የሚናገረው ንግግር፣ የሚፈጥረው ዕርቅ ክብር የሚኖረው በርሱ ዘንድ ቦኩ (በትረ ሥልጣን) ስላለ ነው። በሌላ በኩል ቦኩ የከበረ ንዋይ ነው ማለት ነው። የከበረ ንዋይ ያላት ሴት ከሌሎች ሰዎች ልዩ ክብር የሚኖራት የከበረ ንዋይ ስላላት ነው። ከለቻ ይዘው የጋብቻ ጥያቄ የተሔደ ዕለት ልጃገረድ የሚሰጣቸው ለከለቻው ክብር ነው። ይህም ማለት የከበረ ንዋይ ያለው ሰው በከበረ ንዋዩ ስም የተለየ ክብር ይጎናፀፋል ማለት ነው። በጥቅሉ እነዚህ የከበሩ ንዋያት በብዛት የሚውሉት ለምንድነው? ከተባለ ታርክን መንገርና ክብር ያላቸው መሆናቸው አንድ እውነታ ሆኖ ሳለ ትልቁ ጥቅማቸው ግን እርቅና ሰላም ነው (አቶ ሲሳይ ቡልቡላ፣ 02/10/2010 ዓ.ም ደ'ክ ኮራ)።*

ለዕርቅ መቋጫነት ከፍተኛ ሚና ያላቸው የከበሩ ንዋያት በሚከተለው ትንታኔ መሠረት ቀርበዋል። ተገልፀዋል።

**ሀ. ቦኩ/ Bokkuu:-** በቱለማ ገዳ ሥርዓት ውስጥ “ቦኩ” የሥልጣን ምልክት ሲሆን፣ በትረ ሥልጣን ማለት ነው። ይህን በትረ ሥልጣን የሚይዘው ደግሞ በፕሬዝዳንትነት የተመሰለው አባ ቦኩ ነው። ይህ በትረ ሥልጣን ተፈጥሯዊ[19] እና ሰው ሰራሽ ተብሎ በሁለት ዓይነት ይከፈላል። ይህ ንዑስ ርዕስ ሰው ሰራሽ የሆነውን ቦኩ የሚመለከት ሲሆን የራሱ የሆኑ የማበልፀጊያ[20] ሂደት እና መገለጫ ባህርያት አሉት። ቦኩ ከብኩርና ጋር የተያያዘ ነው። አባ ቦኩ የሚሆነው የነገዱ ወይም የጎሣው በኩር (Angafa) የሆነው ሰው ነው፤ ይህም የአባ በኩነት ሥልጣን እንደ አባ ገዳ በምርጫ ሳይሆን ከአባት ወደ ልጅ በብኩርና የሚተላለፍ ነው። ብኩርና በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ትልቅ ክብር ያለው ሲሆን ከቱለማ አንፃር የራሱ ደረጃ አለው፣

> *ቦኩ የሥልጣን ምልክት ነው። ከብኩርና ጀምሮ በደረጃ ይበላለጣል። የቱለማ በኩር ጂዳ ነው። የቱለማ በኩር የሆነው ጂዳ የሚይዘው በትረ ሥልጣንና የጀሌ ጎሣ የሚይዘው በትረ ሥልጣን ወይም የኦቦ ጎሣ የሚይዘው ወይም የበቾ ጎሣ የሚይዘው አንድ አይደለም። በቱለማ ደረጃ ትልቅ ክብር ያለው የጂዳ በትረ ሥልጣን ነው (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ - በትርጉም የቀረበ)።*

ይህም ማለት ቱለማ ዳጪ፣ በቾ እና ጀሌ የተሰኙ ልጆች እንዳሉት ተገልጿል። የቱለማ በኩር ልጅ ዳጪ ነው። የዳጪ በኩር ልጅ ገላን ነው። የገላን በኩር ልጅ ጂዳ ነው ማለት ነው። ጂዳበልዩ ሁኔታ የሚከበርበት ከሦስቱም የቱለማ ልጆች በኩር ስለሆነ ነው። በተመሳሳይ ከሦስቱ የቱለማ ልጆች ታናሽ የሆነውን ጂሌ ብንወስድ በተገለፀው የትውልድ ሐረግ መሠረት ጐና፣ ጉሳ፣ ሎያ፣ ወሬ፣ ሲባ፣ ጊንዶ የሚባሉ ስድስት ልጆች አሉት። ከስድስቱ ልጆች ጐና በኩር ነው። በቱለማ ዘንድ የጂዳ በትረ ሥልጣን ትልቅ ክብር እንዳለው ሁሉ፣ በጂሌ ዘንድ ደግሞ የጐና በትረ ሥልጣን ትልቅ ክብር አለው ማለት ነው። ይህን መዋቅር እንደ ሀገር ፕሬዝዳንት፣ እንደ ክልል ፕሬዝዳንት፣ እንደ ዞን እና እንደ ወረዳ አስተዳደሪ እንደ ቀበሌ ሊቀመንበር መመሰል የሚቻል ሲሆን ገዳ የራሱን ፌዴራላዊ አወቃቀር ያለው መሆኑን ያመለክታል። ስለሆነም የሦስቱ ቱለማዎች በኩር እንደ ፕሬዝዳንት በትረ ሥልጣን፣ እንደ ሀገር ሊወከል ይችላል። በትረ ሥልጣን ወይራ ባለበት ሥፍራ ከወይራ፣ ወይራ በሌለበት ሥፍራ ከዋንዛ ይበለፅጋል። አቶ ማሞ ገዳ እንዳሉት ቦኩ የሚበለፅገው ከመሬት ወጥ ሆኖ ከበቀለው የወይራ ግንድ ነው። የሚያበለፅጉት የገዳ ሥልጣንን የወሰዱ አመራር አባልት ወይም የገዳው አማካሪዎች ናቸው። ሲበለፅግም የወይራ ዛፉ እንዳይጎዳ ከስሩ ወደ ላይ ከፍ ብለው ከመሐል አንድ ክንድ ያህል ይቆርጡታል። ቀሪውን የላይኛውን እና የታችኛውን አካል

---

19 ተፈጥሯዊው ከሰማይ የወረደ ወይም ከዋቃ (ከእግዚአብሐር) ለቱለማ የተሰጠ ስለመሆኑ ይታመናል (አቶ ነገሣ ነገዎ፣ 11/12/2010 ዓ.ም አዱላላ)።

20 ጥናቱ በተካሄደበት በቱለማ ኦሮሞ ባህል በተለይም በምሥራቅ ሸዋ አካባቢ የከበረ ንዋይ በለፀገ (Ulfaan magarfame) እንጂ ተሰራ አይባልም። ተሰራ የሚለው ቃል ይበልጡን በማንኛውም ሰው፣ በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ ለሚሰራው ቁሳቁስ ወይም ዕቃ (Meeshaa, mi’a) የሚያገለግል ሲሆን የከበረ ንዋይ (Ulfaa) የራሱን አገላለፅ እንዳለው ልብ ይሏል።

በተቆረጠው ቦታ የከብት እዳሪ ቀብተው መልሰው ይገጥሙታል፤ አንዳች ማሰሪያ(ጨርቅ) ነገር ይጠመጥሙበታል፡፡ ተመልሶ ይፀድቃል የሚል ሃሳብ አለ፡፡ በዚህ መልኩ አግልግሎት የሰጠው የወይራ ዛፍ ጨርሶውኑ እንዳይጠፋና እንዳይደርቅ ይታከማል ማለት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የገዳ ሥርዓት ሀገር በቀል እውቀትን ተጠቅሞ ዛፎችን እንደሚንከባከብ፣ ለአካባቢ ጥበቃም ትኩረት እንደሚሰጥ የሚያሳይ ነው፡፡ ተከታዩ ቦኩ ከወይራ የበለፀገ ነው፣



ፎቶ 2. ከወይራ የተሰራ ቦኩ የዱግዳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቤተመዘክር መቂ -05/02/2012

አምስቱም የቱለማ ፓርቲዎች[21] የየራሳቸው ቦኩ እና አባ ቦኩ (ፕሬዘዳንት) አላቸው፡፡ በየስምንት ዓመቱ ሥልጣን የሚይዘው ፓርቲ ሲቀያየር፣ አባ ቦኩም ይቀያየራል፡፡ ለምሳሌ 8 ዓመት በሥልጣን ላይ የነበረው የቢርመጂ ቦኩ ይቀመጥና፣ የተተኪው ሜልባ ቦኩ ወይም አባ ቦኩ እና በትረ ሥልጣን በሥራ ይውላል፡፡ በቀረበው ትንታኔ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው ቦኩ የሜልባ ፓርቲ ቦኩ ነው፡፡ ስምንቱን ዓመት ሲጨርስ የተከታዩ የሙደና ፓርቲ ቦኩ ወደ ሥልጣን ይመጣል ማለት ነው፡፡ የሜልባ ፓርቲ ቦኩ ደግሞ በክብር ይቀመጣል፡፡ ከአባ ቦኩው ጋር በክብር ወደ ቤት ይመለሳል፡፡ ለምሳሌ የሜልባ ፓርቲ እንደገና ወደ ሥልጣን የሚመለሰው በ40 ዓመቱ ነው፡፡ በአርባ ዓመቱ ወደ ሥልጣን ሲመለስ ቦኩውን የሚይዘው የአሁኑ አባ ቦኩ ልጅ ነው፡፡ ልጅየው የአባ ቦኩነት ሥልጣን ሲይዝ፣ የአባቱን በትረ ሥልጣን ተጠቅሞ አባ ቦኩ ሊሆን ይችላል፡፡ በትረ ሥልጣኑ በተለያየ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያቶች ቢጠፋ እንኳ አምስቱም ፓርቲዎች እውቅና ሰጥተወት አዲስ ቦኩ ማበልፀግ ይቻላል፡፡ ይህ በትረ ሥልጣን የሚበለፅግበት ሥነ ስርዓት እና በሥራ ላይ የሚውልበት ሂደት እራሱን የቻለ ሂደት አለው፡፡ ኮርማ በሬ ታርዶ፣ ድግስ ተዘጋጅቶ… አምስቱ የገዳ ፓርቲዎች በተገኙበት እውቅና ተሰጥቶት በአዲስ መልክ የበለፀገው በትረ ሥልጣን በሕግ ይሞላል፤ ይመረቃል፤ ይፀድቃል ማለት ነው፡፡ ቦኩ እንደ አባ ቦኩ ትልቅ ክብር ያለው በመሆኑ፣ በክብር ተይዞ በክብር ይቀመጣል፡፡ በኩ በማንኛውም ቦታ አይገኝም፡፡ ወንዝ አይሻገርም፣ አባ ቦኩም እንዲሁ በየትኛውም ሥፍራ አይገኝም፡፡ ወንዝ አይሻገርም፣ ተራራ ለተራራም አይጓዝም፡፡

የአባ ቦኩ ኃላፊነት እና ተግባራት ብዙ ናቸው፡፡  ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡- ከግለሰብ ያለፈና በርካታ ሰዎችን ያሳተፈ ግጭት ከሆነ ቦኩ/ አባ ቦኩ ወጥቶ ያስታርቃል፤ አከራካሪ እና ውስብስብ የሕይወት (የሞት) ጉዳይ ከሆነ አባ ቦኩ ይዳኛል፤ በህይወት ጉዳይ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚያስተላልፈውም አባ ቦኩ ነው፡፡ በተገለፀው መሠረት የገዳ ሰግሊ ሊፈታው ያልቻለው የነብስ፣ የወንጀል እና የዕርቅ

21 በቱለማ ገዳ ሥርዓት መሠረት በየስምንት ዓመቱ ሥልጣን የሚቀባበሉት አምስቱ ፓርቲዎች፡- ቢርመጂ፣ ሜልባ፣ ሙደና፣ ሀልቺሳ፣ ሮበሌ በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡

እንዲሁም ሀገራዊ ጉዳይ በቦኩ እና በአባ ቦኩ እልባት ያገኛል፡፡ የአባ ቦኩ ሥልጣን አሁን ሀገሪቱ ከምትከተለው የፌዴራል ሥርዓት እና የፕሬዜዳንት ሥልጣን ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይኸውም በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት መሠረት የሞት ፍርድ የሚያፀድቁት የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ናቸው፡፡ አባ ቦኩም እንደሁ የመጨረሻውን የሞት ጉዳይ ወይም የደም ካሣ (ጉማ)፣ ታላላቅ ሀገራዊ እና ህዝባዊ ጉዳዮችን ይወስናሉ፡፡ በውሳኔ ይመሳሰል እንጂ አባ ቦኩ ግን የሞት ፍርድ አያስተላልፍም፡፡ ጉዳዩ በእርቅ እና በካሣ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡ ይህ የክብር እና የሥልጣን እንዲሁም የማህበራዊ እና እምነታዊ እሴት መግለጫ ትዕምርት የሆነው ቦኩ በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠው በህብረተሰቡ ዘንድ ዕርቅ ለማውረድ እና ሰላምን ለማስፈን ካለው ትልቅ ሚና አንፃር ነው፣ "ለዕርቅ ሲባል ከተቀመጠበት የክብር ቦታ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ በሕዝቡ እምነት መሠረት የሚቱ ወገን ወይም ለፀብ የሚነሳሳው ወገን ያንን ቦኩ የሚያይ ኮሆነ ዝም ይላል፤ ለበቀል መነሳሳቱን ያቆማል (መሉጌታ፣ 1997፡ 72)፡፡

በዚሁ መሠረት ቦኩ በህብረተሰቡ ዘንድ ካለው ክብር የተነሳ መበቃቀልን ያቆማል፤ ዕርቁም ወዲያውኑ እንዲፈፀም ያደርጋል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል በቱለማ የትውልድ ሐረግ ውስጥ አባ ቦኩ በኩር ስለሆነ "ሀዩ/ Hayyuu" በሚል ስያሜም የሚጠራ ሲሆን ገዳው እና አባ ገዳው አቅጣጫ እንዳይስት ከበላይ ሆኖ ምክር ይለግሳል፡፡ በቱለማ ገዳ ውስጥ በትረ ሥልጣን የላዕላዩ የሥልጣን አካል ምልክት በመሆኑ ትልቅ ክብር አለው፤ አባ ቦኩም እንዲሁ የላቀ ክብር አለው፡፡ ስለሆነም ዕርቅ ለመፍጠር እና ሰላም እንዲሰፍን ቦኩም ሆነ አባ ቦኩ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

**ለ. ከለቻ/ Kallachaa:-** በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ከፍተኛ ክብር ያለው የከበረ ንዋይ ነው፡፡ ከለቻ ሁለት አይነት ያለው ሲሆን፣ አንደኛው እና የመጀመሪያው በኦርቶዶክስ እምነት እንደሚታወቀው የፅላት ዓይነት ሚና ያለው ነው፡፡ በዋቄፈና አስተምህሮ መሠረት ኃይማኖታዊ ሚና ያለው በመሆኑም ከቅድስና ጋር የተያያዘ ንዋየ ቅዱስ ነው፡፡ ሁለተኛው የግንባር ከለቻ (Kallacha Addaa) ወይም የሥልጣን ምልክት ከለቻ (Kallacha Aangoo) በመባል ይታወቃል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የዋቄፈና እምነት እና የዕርቅ መቋጫ የሆነው ከለቻ ነው፡፡ የዋቄፈና እምነት ከለቻ ይበልጡን ከእምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዋቃ ለሰው ልጅ ለዚያውም ለተቀደሰ ንፁህ ሰው የተሰጠ ነው የሚባለው ከለቻ ከቅድስና ጋር ተጣምሮ የሚታይ በመሆኑ የላቀ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ይህ የከበረ ንዋየ ቅዱስ ከሰማይ እንደሚወርድ ይነገራል፣

> *በመብረቅ መልክ ይወርዳል፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህ መብረቅ ሲወርድ ያረፈበት ቦታ መሬቷ ትጎደጉዳለች (ትሰነጠቃለች)፡፡ ሰው ይሞታል፣ የተለያየ ነገር ይበላሻል፡፡ በቅድስናቸው የሚወርድላቸው ሰዎች ግን ቤታቸው እንኳ አይቃጠልም፣ ሰውም አይጎዳም፣ ሰዎች በተኙበት ሥፍራ በሰዎች መካከል ይወርዳል፡፡ ይህን በቅድስና የመጣውን የከበረ ንዋይ የላም ወተት ጠብ አድርገውበት አላምደው ይይዙታል፡፡ እግዚአብሔር ነው ገራም አድርጎ ያወረደው ማለት ነው፡፡ ዝም ብሎ ያለ ቅድስና ከወረደ ግን ሰውን ይገድላል፡፡(አቶ ኀበና ሲዳ፣01/10/2010ዓ.ም ቢሾፍቱ - በትርጉም የቀረበ)፡፡*

ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ከለቻ ከህብረተሰቡ ኃይማኖታዊ እና ትውፊታዊ እሳቤ ጋር የተሰናሰለ ነው። በቁጣ የወረደው መብረቅ አደጋን ስለሚያስከትል፣ መብረቅ የወረደበት ሰው ወይም ቤተሰብ በፈፀመው አንዳች ግፍና ኃጢያት ምክንያት ዋቃ ተቆጥቶታል ተብሎ ይገመታል። በህብረተሰቡ ዘንድ መብረቅና በረዶ የዋቃ ቁጣ ነፀብራቅ ናቸው ተብለው ይታሰባሉ። መፍትሔውም ከነቢይ (Raagaa) ተጠይቆ የሥርየት (Faloo) መስዋዕት ማከናወን ይሆናል። ስለሆነም መብረቅ አንድም የእግዚአብሔር ቁጣ ምልክት ነው። በሌላም በኩል የቅድስና ትዕምርት ነው። ከሰማይ የወረዱ የሚባሉት ንዋየ ቅዱሳት ከለቻ ብቻ ሳይሆን፣ በቀዳሚው ርዕስ እንደታየው ቦኩ፣ ጫጬ… ሊሆኑ ይቻላሉ። የሚወርዱበት ትውፊታዊ እና ኃይማኖታዊ ገድል ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን የዋቄፈና እምነት ትዕምርት የሆነው ከለቻ በቱለማ ኦሮሞ ባህል እና የዋቀፌና እምነት ውስጥ የጐላ ሚና እንዳለው ይታወቃል። የጐላ ሚና ሊኖረው የቻለው እንዴት ነው? ተከታዩ ሃሳብ ከቀዳሚው ጋር ተመጋጋቢ ነው፣

> *በኦሮሞ ዘንድ የከበሩ ንዋያት ተብለው ከሚታወቁት መካከል ከለቻ አንደኛውና ከፍተኛው ነው። በንፅፅር ቢያመሳስሉት በኦርቶዶክስ ፅላት እንደሚባለው ዓይነት ደረጃ ይታያል። ኦሮሞ ያለው የመጀመሪያው ከለቻ ከሰማይ የወረደ ነው። ከለቻ ከሰማይ የወረደ ነው ይባላል። ክብሩ በተለየ ሁኔታ የሚታየው ይህ ከሰማይ የወረደው ከለቻ ነው። ይህን ሁኔታ ኦሮሞ ወደ መንፈሳዊ ኃይል ይቀይረዋል። የቱለማ ከለቻ እንደ ቦረና ከለቻ በግንባር ላይ የሚታሰር አይደለም። የቱለማ ከለቻ ቤተ እምነት ውስጥ ነው የሚቀመጠው (አቶ ማሞ ገዳ፣21/01/2012 ዓ.ም አዳማ)።*

እንደ መረጃ አቀባዩ ገለፃ ከሰማይ የወረደው ከለቻ መንፈሳዊ ኃይል (humana ayyaantummaa) ያለው ሲሆን፣ የተባዕት መንፈሳዊነት ምልክት (mallattoo ayyaantummaa dhiiraa) ነው። ‘አያንቱማ’ የሚለው የአፋን ኦሮሞ ቃል ገላጭ ሲሆን አያና ማለት ጠባቂ መልዓክ ማለት ነው። በኦሮሞ ባሕል እያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መላክ እንዳለው ይነገራል። በሌላ በኩል መልዓክ /መለኮት/ መንፈስ ማለት ሲሆን እንደ አገባቡ የተለያዩ ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል። የቱለማ ከለቻ በኦሮቶዶክስ ኃይማኖት እንደሚታየው ቤተ ክርቲያን መሰል ቤተ እምነት (Galma/ገልማ) ተሰርቶለት በክብር ይቀመጣል እንጂ በማንኛውም ጊዜ፣ በማንኛውም ቦታ የሚገኝ አይደለም። ቤተ እምነት/ ቤተ ዋቃ (Galma) የቱለማ ኦሮሞዎች እግዝአብሔርን የሚያመልኩበት፣ የሚያመሰግኑበት የእግዚአብሔር ቤት እንደማለት ሲሆን እራሱን የቻለ አሰራር አለው (አባ ሙዳ አበበ ኃይሉ፣ 02/02/2012 ዓ.ም ኡዴ - ገርቢቻ)። የቃሉ ችሎት በነዚህ ቤተ እምነት ይካሄዳል። የቱለማ ከለቻ የፅላት ዓይነት ወግና ማዕረግ ያለው ነው። ለትላልቅ ሀገራዊ ጉዳዮች፣ ለእርቅ፣ ለተለየ ክብረ በዓል፣ ለአዳ ነቤ ጉዞ፣ ለጉዲፈቻ፣ ለጋብቻ፣ የጉማ ሥርዓትን ለማስፈፀም ወዘተ… ትልቅ ለሆነ ሕዝባዊ ጉዳዮች ካልሆነ በቀር ከገልማው አይንቀሳቀስም። በግልፅም አይታይም። ለመንፈሳዊ ተግባራት የሚፈለግ ነው ስለሚባል ብዙውን ጊዜ በሚዲያ እንደሚሰማው ልክ እንደ ፅላት ለስርቆት እንደሚጋለጥ ሁሉ ይህም የቱለማ ከለቻ ለስርቆት የተጋለጠ ነው ሲባል ይደመጣል። ነገር ግን ሰው ሰራሽ ካልሆነ በቀር ከሰማይ ወረደ የሚባለው ከለቻ በቀላሉ የሚደፈር አይደለም ይባላል፣

> *ለስርቆት የሚጋለጠው አርቴፊሻል[22] ነው፡፡ ከለቻ ለመውሰድ ብለው ተዝለፍልፈው፣ ሳይሳካላቸው ቀርቶ ወድቀው ጥለው ካጠገቡ የጠፉ ሰዎች እናውቃለን፡፡ በሀገራችን ይህን ከለቻ ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡ ይህ ከለቻ ዋጋ ያወጣል ሲባል ሰምተው ሄዱ፤ ሰዎቹ ሽፍታ ናቸው፡፡ ባለ ከለቻውን 'ይህን ከለቻ ለመውሰድ ነው የመጣነው አሉት'፣ 'ሂዱ ውሰዱ' ብሎ ተዋቸው፡፡ ሰዎቹ እዚያው ተዝለፍልፈው ወድቀው፣ የኋላ ኋላ አቅቷቸው ተመለሱ፡፡ ኦሪጅናል የሆነው ከለቻ እራሱን ይከላከላል (አቶ ማሞ ገዳ፣ 21/01/2012 ዓ.ም አዳማ)፡፡*

በመለኮታዊ ኃይልና ተዓምር እራሱን በራሱ ከስርቆት ይከላከላል ማለት ነው፡፡ በዚሁ የመለኮታዊ ኃይል እሳቤ መሠረት ከለቻ ከንፅህናና ከቅድስና ጋር ይያያዛል፡፡ በአንድ የፀሎት፣ የምስጋናና የምልጃ ለምሳሌ ዝናብ ጠፍቶ ከዋቃ ዝናበ ምህረት ለመለመን በሚደረግ የፀሎት ስነስርዓት ላይ ከለቻን ይዞ ለመውጣት (ይዞ ለመገኘት) የሚሸከመው ሰው ባለ ከለቻ (Abbaa Kallachaa/አባ ከለቻ) የሚጠነቀቃቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከለቻ መሸከም የሚቻለው ሰውን ያልገደለ፣ በነብረተሰቡ ዘንድ በግብረገብነት እና በመልካም ስራው የታወቀ ግለሰብ መሆን አለበት፡፡ ከለቻውን ከሚሸከምበት ዕለት አስቀድሞ ከሕጋዊ ሚስቱም ጋር ቢሆን ቢያንስ ቢያንስ ለሦስት ቀናት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት የተቆጠበ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል እንደተገለፀው የራሱ ትውፊታዊ እና እምነታዊ ደንብ አለው ማለት ነው፡፡ ከለቻ በቱለማ ኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ልዩ ክብር አለው፡፡ ከንፅሕና፣ ከቅድስና ከእምነት ጋር የተያያዘ በመሆኑም ይፈራል፤ ይከበራል፡፡ የከለቻን ክብር መዳፈር፣ ከለቻ በሚገኝበት ገልማ ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ መፍጠር እንደ ትልቅ ነውር ይቆጣራል፡፡ በግለሰቡ ብሎም በቤተሰቡ ላይ አደጋ፣ መዓት፣ እልቂትና ችግር ያስከትላል ተብሎም ይታመናል፡፡ ከለቻ እና ጫጩ ብዙውን ጊዜ በአንድ ስነስርዓት ላይ ይታደማሉ፡፡ ለፀሎት፣ ለእርቅ ወዘተ. በጋራ የሚገኙበት ሁኔታ ይታያል፡፡ አባ ከለቻው ከለቻ ሲይዝ፣ ሚስትየው ደግሞ ጫጩ ይኖራታል፡፡ ትይዛለች፡፡ ስለሆነም ሁለቱ የከበሩ ንዋያት ህብር ናቸው፣

> *ከለቻ እና ጫጩ ብዙውን ጊዜ አብረው ነው የሚሄዱት፡፡ ከለቻ ባለበት ቦታ ጫጩ አለ፡፡ ከለቻ እግዚአብሔር በመረጠው ወይም ገዳም/ገራም የሆነ ሰው፣ የተከበረ ሰው ዘንድ ነው የሚቀመጠው፡፡ ባለ ቤተየው (ባለ ከለቻው) ከለቻ ካለው፣ ሚስትዋ ደግሞ ጫጩ ትሸከማለች ማለት ነው፡፡ ከለቻና ጫጩ ፈፅሞውኑ ተነጣጥለው አይታዩም፡፡ ከለቻ ለትላልቅ ጉዳዮች ሰው ሲጣላ፣ ሀገራዊ ግጭት ሲኖር፣ ልዩ ልዩ ችግሮች ሲኖሩ፣ ዝናብ በጠፋ ጊዜ፣ እንስት ልጅ ስታጣ (መካን ስትሆን) ወጥቶ ፈጣሪን ለመላመን የሚያገለግል ነው (አቶ ደሜ አብቹ፣ 21/01/2012 ዓ.ም አዳማ)፡፡*

በጥቅሱ መሠረት ከለቻው ብቻ ሳይሆን አባ ከለቻ - ባለ ከለቻውም የተከበረ ነው፡፡ እንደተባለው በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ከለቻ ትልቅ ክብር ስላለው ጠብና ግጭት፣ የሞት ጉዳይና የካሣ ስነስርዓት፣ የዕርቅ ስነስርዓት፣ በሰላማዊ መንግድ መፍትሄ እንዲያገኝ ትልቅ ድርሻ አለው፣ ከለቻ በኦሮሞ ባህል ወግና እምነት ውስጥ ባለው

22. በጥቅሱ ውስጥ የተካተቱት አርቴፊሻል (Arteefishaalii/ አርቴፊሻሊ) እና ኦሪጅናል (Originaalii/ ኦሪጅናሊ) የእንግሊዝኛ ቃላት ናቸው፡፡ ነገር ግን በአማርኛም በአፋን ኦሮሞም የተለመዱ ናቸው፡፡

ታላቅ ሥፍራ እንደሚከበር ሁሉ በቱለማ ኦሮሞ ዘንድም በተመሳሳይ መልኩ ለዕቀርሰላም ማውረጃነት ከፍተኛ ሥፍራ ያለው ነው (ዓለማየሁ፣2000ዓ.ም፡ 232)፡፡

ዕርቅ ሲባል የተጣሉ ሁለት ሰዎችን ብቻ ማስታረቅ ማለት አይደለም፡፡ ለጋብቻ ያልተግባቡ ወይም ፍቃዳቸውን ያላሳዩ ቤተሰቦችም በዚሁ ከለቻ ይለመናሉ፤ ፍቃዳቸውን እንዲያሳዩም ይጠየቃሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ በሽምግልና የተጠየቀ እና በተለያዩ ምክንያቶች የልጅቷ ቤተሰቦች ፍላጎት እና ፍቃድ ባለማሳየታቸው እምቢ የተባለ የጋብቻ ሂደት እንኳ በከለቻ ከተጠየቀ እምቢ አይባልም፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ለምሳሌ ግለሰቡ የገዳ ሥርዓትን ለማሟላት አልያም ከኢኮኖሚ ችግር የተነሳ (አግቢው ሙሽራ ወይም ልጅየው ቤተሰብ ከሌለው፣ መደገስ ካልቻለ) ወዘተ. በድንገት ወይም በአጭር ጊዜ የሚፈፀምን ጋብቻ በስኬት ለማከናወንም ያገለግላል፡፡ በቱለማዎች ዘንድ የከለቻ ጠቀሜታ የሚለካው ግጭትን ለማስወገድ፣ ሰላም እና እርቅ ለማውረድ ካለው ትልቅ ሚና አንፃር ነው፡፡ ለምሳሌ ሁለት ሰዎች ቢገዳደሉ የገዳይ ወገን (ጉሣ) ከለቻ ይዘው፣ የሟች ወገንን ይቅርታ ይጠይቃሉ፤ ጉዳዩም በጉማ (የደም ካሣ) ስነስርዓት እልባት እንዲያገኝ በከለቻው ይማፀናሉ፡፡ በዚህ የከለቻ ተማፅኖ የዕርቅ ሂደቱ ይጀመራል፤ ችግሩም በሰላም ተፈቶ እልባት ያገኛል፡፡ ከለቻ ካለው ክብር አንፃር አልታረቅም እምቢ የሚል ወገን የለም፡፡

ከለቻ እምነታዊ ትዕምርት መሆኑን የጠቀሰው ሙልጌታ (1997፡ 72)፣ ህብረተሰቡ ስለ ከለቻ ያለውን አተያይ እንዲህ ገልጿል፣ በመብረቅ ተመስሎ 'ዋቃ/ አምላክ' ለኦሮሞ የላከው የእምነቱ ትዕምርት ነው ይባላል፡፡ በሌላ አባባል ኦሮሞ በአንድ እምነት ጥላ ስር እንዲተዳደር 'ዋቃው' የራሱን መንፈስ አሳርፎበት የላከው የእምነቱ መሳሪያ /religious symbol/ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ የፍቅርና የሰላም ማውረጃ ትዕምርት ነው ይላሉ፡፡ ስለዚህ አምላክ ለፍቅርና ለሰላም መፍጠሪያ፣ ለእርቅ መገልገያነት የላከውን ረግጦ ግጭቱን የሚያባብስ ሰው ከአምላክ /ከዋቃ/ ጋር የተጣላ ተደርጎ ይገመታል፡፡ የሟች ወገኖች እርቁን እንዲቀበሉት ሲባል በእግዚኦታው አውዳዊ ክዋኔ ላይ ከሚያቀርቡት እምነታዊ ትዕምርቶች አንዱ ነው"፡፡ በተመሳሳይ ታቦር (2007፡220) "ከለቻ ለኦሮሞ ሕዝብ አገልግሎት ከአንድ አምላክ (ዋቃ) ከሰማይ የወረደ፣ የእርቅ ምልክት ነው ብለው ስለሚያምኑ ትልቅ ክብር አለው" ሲል አመልክቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ግጭት እንዳይባባስ፣ መገዳደል፣ መበቃቀል እንዲሁም ስር እየሰደደ የሚሄድ የደም መመላለስ - ጥቁር ደም… እንዳይኖር ከለቻ የማይተካ ሚና አለው፡፡

**ሐ. ጫጬ/ Caaccuu: -** በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ ለዕርቅ መቋጫነት ከሚውሉ የከበሩ ንዋያት መካከል እንደ ከለቻ ሁሉ ጫጬም በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ተለፍቶ ከተዘጋጀ የከብት ቆዳ - "ነት" እና ዛጎል… የገዳ፣ የባህላዊ እና የዋቄፈና እምነት እሳቤዎችን መነሻ በማድረግ የሚዘጋጅ ሲሆን ቅድስና አላቸው ተብለው በሚመረጡ ዕድሜያቸው የገፋ ሴቶች አማካኝነት የሚበለፅግ ነው፣ "ጫጬን ሁሉም ሰው ሊያበለፅገው አይችልም፡፡ ህግ አለው፡፡ ጫጬን የምታበለፅገው በቤት ውስጥ የተወሰነች፣ የኑሮ ዓለሟን የጨረሰች ሴት ናት" (የቀድሞ አባ ገዳ በየነ ሰንበቶ፣ 11/12/2011ዓ.ም ቢሾፍቱ)፡፡

በቤቷ የተወሰነች፣ የተሰበሰበች የሚሉት ቃላት ከንፅህና ጋር የተያያዙ አገላለፆች ሲሆኑ፣ ግብረ ሥጋ የማትፈፅም ከዚህም ድርጊት ጋር ምንም ግንኙነት የሌላት፣ ይህንንም ተራክቦ በእድሜ ምክንያት የተላለፈች ፈጣሪዋን ብቻ የምታመለክ ንፁህ ሴት (አሮጊት) ለማለት ተፈልጎ ነው። ጫጬና ጨሌ ከቅድስናና ከንፅህና ጋር የተቆራኙ ንዋየ ቅዱሳት ናቸው። ከቅድስና ጋር በተያያዘም የዋቄፈናን የእምነት ሥርዓት በሚያውቁ ሰዎች ሊበለፅግ ይችላል። በውስጡም የዋቄፈናን እምነት እና ማህበራዊ እሳቤዎችን የያዘ ነው።



ፎቶ 3. በአቶ ነገሣ ነገዎ ቤት- ቦሮ/ Boroo [23] የሚገኝ ጫጬ-(11/12/2010 ዓ.ም አዱላላ)።

በንዑስ ርዕሱ እንደተገለፀው ጫጬ በዋናነት ለዕርቅ መቋጫነት የሚውል ነው። በዕርቅ እና በግጭት አፈታት ስነስርዓት ወቅትም ከከለቻ፣ ከቦኩ እና ከሌሎች ተዛማጅ የክበሩ ንዋያት እንዲሁም ባህላዊ እሴቶች ጋር በአንድነት ይገኛል፣ "የተገዳደሉ ሰዎች እንኳ በዚህ ጫጬ ይታረቃሉ። የተገዳደሉ ሰዎች ሲታረቁ ጫጬ አውጥተው፣ ፈረስ ለጉመው፣ ሄደው እግዚኦ?! ይላሉ። ልጃገረድም ድፍን ቅል ትሸከማለች" (ወ/ሮ ሎኒ መርጋ፣ 27/06/2011 ዓ.ም ጎራ ለማን)።

በከለቻ፣ ጫጬ፣ በተለጎመ ፈረስ እና በድፍን ቅል የሚለመኑ የሚች ቤተሰቦች፣ ሰው ሞቶብናል በቀላችንን ሳንወጣ አንታረቅም ብለው እምቢ አይሉም። ምክንያቱም እርቅን እየጠየቁ ያሉ ሰዎች የክበረ ንዋይ ይዘዋል። የክበረ ንዋይን ተዳፍሮና ተላልፎ አልታረቅም የሚል ሰው የለም። በገዳ ህግ መሠረት የገዳይ ጎሣ፣ ለሚች ጎሣ (ቤተሰብ) የደም ካሣ (ጉማ) ይከፍላል። ቀደም ሲል በዚህ መጣጥፍ ጽሑፍ እንደተጠቀሰው ዕርቅ ሲባል ግጭትን ብቻ የተመለከተ ሳይሆን ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ተፈጥሯዊ እና ስነልቦናዊ ችግሮችን መፍታት እንዲሁም ዋቃ ለሰው ልጅ ዝናበ ምህረቱን እንዲያወርድ መፀለይ በራሱ በማህበረሰቡ አተያይ ዕርቅ ነው። ከነዚህም አገልግሎቶች መካከል አንዱ በጫጬ የጉዲፈቻ ልጅ መጠየቅ ነው፣

23 "ቦሮ/Boroo" የቤት ማዕከላዊ ሥፍራ፣ የክበሩ ንዋያት የሚቀመጡበት (የአውደ ምህረት) ቦታ። ቦሮ በሌላ ትርጉሙ የፀሐይ መውጫ፣ የምሥራቅ አቅጣጫ፣ ወጋገን ወይም መርሐ ንጋት ሊሆን ይችላል።

> *ልጅ ያጣ ቤተሰብ ይህን ጫጩ ተሸክሞ ልጅ ያገኝበታል፡፡ ጫጩ ወጥቶ አያጣም፡፡ ልጅ የሌላትን ሴት ይህን ጫጩ አሸክመው፣ የከበረ ንዋይ ወጥቶ ልጅ ከሚለምኑበት ቤተሰብ ደጃፍ ይቀመጣሉ፡፡ ልጃችሁን ስጡን ብለው ይለምናሉ፡፡ ልጅ ያጣችው ሴት፣ ልጅ ያላትን ሴት ልጅሽን ስጪኝ ብላ ትለምናታለች፡፡ አንቺ ባለ ፀጋ ነሽ፤ እኔንም ባለፀጋ አድርጊኝ፤ እኔ ያጣሁ ነኝ (ልጅ የሌለኝ ነኝ) ብላ ትለምናለች፡፡ ከዚያም ልጅ ይሰጧታል፤ አይከለክሏትም (ወ/ሮ ሎኒ መርጋ፣ 27/06/2011 ዓ.ም ጎራ ለማን -በትርጉም የቀረበ)፡፡*

ለጉዲፈቻ ልጅ ጥየቃ ከለቻም ተመሳሳይ ሚና እንዳለው ተጠቅሷል፡፡ እንደ ሁኔታው አብረውም ሆነ ተነታጥለው ለዚሁ ዓላማ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ ከለቻና ጫጩ… ወጥተው በስኬት ይመለሳሉ እንጂ ሳይሳካላቸው አይመለሱም ማለት ነው፡፡ ለጉዲፈቻ የተጠየቀው ልጅ ይሰጣል፤ አይከለክልም፡፡

ከተከለከለ ልጅው ክፉ አጋጣሚ ይደርስበታል፤ በሰላም አያድግም፤ ካደገም ጤናማ አይሆንም፤ አንዳች እክል ይገጥመዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ልመናው ተሳክቶላቸው የጉዲፈቻውን ልጅ የወሰዱ ቤተሰቦችም እንደራሳቸው ልጅ ተንከባክበው፤ የልጅነት መብቱን ጠብቀው ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ልጅየው በማደጎ ከመጣ በኋላ ባልና ሚስት ሌላ ልጅ ቢወልዱ እንኳ በኩር የሚሆነው በጉዲፈቻ የመጣው ልጅ ነው፡፡ ከአብራካቸው ካገኙት ልጅ ለይተውና አድሎ ፈፅመው አያሳድጉትም፡፡ እንዲህ ካደረጉም የገዳ ህግ የሚወስነውን ቅጣት መቀጣት ማለትም ልጅየው ወደ ቤተሰቡ እንዲመለስ እስከማድረግ በዘለለ ይህን መሰሉን አድሎ የፈፀመው ቤተሰብ ኃጢያቱን ይቀበላል፤ ከዚህ ልጅና ከዚህ መድሎ በኋላ የተገኘውም ልጅ መቅኖ ቢስ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ከዚሁ አንፃር ጫጩ ወይም ከለቻ ልጅ መውለድ የተሳናት አንዲት መካን ሴት፣ ትዳሯ ሳይፈርስ ልጅ እንድታገኝና እንድታሳድግ፣ የልጅየው መብት እንዲጠበቅ፣ ማህበራዊ ህይወት እንዳይናጋ የማድረግ አቅም አላቸው፡፡ የህዝቡን ትውፊትና እምነትም በውስጣቸው የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር ልጅ የመውለድ ዕድሜ ውስጥ ያለች አንዲት ሴት በተለያየ ምክንያት ልጅ መውለድ ካልቻለች፣ ልጅ የመውለድን ፀጋ/በረከት ዋቃ እና አቴቴ (አቴቴ ማሪም/ Ateetee Maaram) እንዲሰጧትም፤ ልጅም እንድትወልድ በዚሁ ጫጩ ይለመንላታል፡፡ የፀሎት ስነስርዓት ይካሄድላታል፡፡ ጫጩ  አንድም ፈጣሪን ለመለመን፣ አንድም ለጉዲፈቻ፣ አንድም እርቅ ለመፈፀም ይጠቅማል፡፡ ጠቀሜታውም እንደ ከለቻ ሁሉ ፈርጀ ብዙ ነው፡፡ የገዳ ሥርዓት፣ የዋቄፈና እምነት፣ የእንስትነት፣ የዕርቅ መቋጫ እና የግጭት ማስወገጃ ትዕምርት የሆነው ጫጩ ብዙውን ጊዜ በህብረተሰቡ ዘንድ ክብር እና ቅድስና … ባላቸው ሴቶች የሚያዝ ስለመሆኑ በመስክ በነበረን ምልከታ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ቀጣዩ ወዴቻ ነው፡፡

**መ. ወዴቻ**

በተለምዶ “Waddeecha/ወዴቻ” የሚባለው “Ulee Waddeechaa/የዋንዛ በትር” ነው፡፡ ነገር ግን ወዴቻ እራሱን ችሎ የዛፍ ዓይነት ሲሆን፣ ዋንዛ ማለት ነው፡፡ ዋንዛ በቱለማ ኦሮሞ ዘንድ በእጅጉ የተከበረ የዛፍ ዓይነት ነው፡፡ በገዳ ሥርዓት ትልቅ ክብር ካላቸው፣ ህግ ከተደነገገላቸው ሀገር በቀል የዛፍ ዓይነቶች መካከል አንዱ

ነው። በርግጥ በዚህ ልክ የሚጠቀሱ እንደ ኦዳ እና ዝግባ አይነት ሌሎች ሀገር በቀል ዛፎችም አሉ። ግና የየራሳቸው ድርሻ፣ የየራሳቸው ቦታና ጊዜ አላቸው። ተከታዩ ጥቅስ ይህንኑ ሃሳብ ያስረዳል፣

> *በገዳ ሕግ መሠረት የጋብቻ ስነስርዓት ለመፈፀም ሲሄዱ ዋንዛ ይዘው ነው የሚሄዱት። በትረ ሥልጣን እንኳ የሚበለፅገው ከዋንዛ ነው። ዋንዛ ከሁሉም ዛፎች በኩር ነው። ዋንዛ ወይራ፣ ዝግባ፣ ኦዳ፣ ሰፋ አለ። ሁሉም ቦታ ቦታ አላቸው። ዋንዛ "ከሰው መርጦ ለሹመት፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት" የተባለለት ነው። ዋንዛ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው (የቀድሞ አባ ገዳ በየነ ሰንበቶ፣ 11/12/2011 ዓ.ም ቢሾፍቱ)።*

በዚህም ሳቢያ ወዴቻ በቱለማ ኦሮሞ ባህል ውስጥ ትልቅ ክብር አለው። አገልግሎቱም ብዙ ነው። ከነዚህም መካከል በመረጃ አቀባዩ የተጠቀሰው ለጋብቻ ጥየቃ ሽማግሌ ሲላክ የሚያዝ መሆኑ አንዱ ነው። በቀድሞው ጊዜ ለጋብቻ የሚላኩ ሰዎች ስምንት ነበሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የዋንዛ በትር የያዙ አራት ሽማግለዎችን መላክ እየተለመደ ነው። አራት ሽማግሌዎች፣ አራት የዋንዛ በትር በድምሩ ስምንት ይሆናሉ። ስምንት መሆኑ የቀድሞውን ባህል መልሶ የሚያሟላ ይሆናል ማለት ነው። አራቱ ሰዎች የተወከሉት በዋንዛ በትር ስለሆነ፣ ዋንዛ በሰው ቦታ ሆኖ ጋብቻ የማስፈፀም ውክልና አለው ማለት ነው። አራት ሰው፣ አራት የዋንዛ በትር በድምሩ ስምንት የመሆናቸው ምስጢር ደግሞ የገዳ ስምንቱን ዓመታት ይወክላል። የዋንዛ በትር በህብረተሰቡ ዘንድ ካለው ክብር አንፃር ቦኩ፣ ከለቻ ሲንቄ ይዘው የሚጓዙ ሰዎችን ከፊት ለፊት ማቋረጥ ነውር እንደሆነ፣ ባለ ወዴቻዎችንም በተመሳሳይ በአክብሮት ቆሞ ማሳለፍ እንጂ ማቋረጥ አግባብ አይደለም፤ ነውር ነው። ምክንያቱም ዋንዛ የክብር ምልክት ነው።

የዋንዛ በትርን የሚይዙ ጉልማሶች፣ አረጋውያን፣ በገዳ የፓርቲ መዋቅር ውስጥ ያሉ አባ ገዳዎች፣ አያንቱዎች፣ አባ ወዴቻ (Abbaa Waddeechaa) በሚል መጠሪያ ይታወቃሉ። በዚህም ሳቢያ የዋንዛ በትር ለሚይዘውም ሰው የክብር መግለጫ ነው፤ ዋንዛ በራሱም ክቡር ነው፣

> *ይህን የዋንዛ በትር በመስቀል በዓል ጊዜ፣ ደመራ በሚበራበት ጊዜ ተይዞ ይወጣል። ችቦ ማብራት ወደ ብርሃን መሄድን ያሳያል። የዋንዛ በትር ቂቤ ተቀብቶ፣ የጣሪያ ጭስ ጠግቦ፣ ቀልቶ ወይም ጠቀሮ ይወጣል። ለደረሰ ልጅ ሚስት ያጋቡበታል፣ ዕርቅ እና የከበረ ቦታ ይሄዱበታል። ይህ የዋንዛ በትር ክቡር (የተከበረ) ነው (አቶ በቀለ ቢፍቱ፣ 03/10/2010 ዓ.ም ደ'ከ ኮራ - በትርጉም የቀረበ)።*

የዋንዛ በትር ተይዞ የተጠየቀ ጋብቻ ብዙውን ጊዜ እምቢ አይባለም፤ አይከለከልም። የዋንዛ በትር በኀብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ ግምትና ክብር ስለሚሰጠው ለአባ ወዴቻዎቹም ሆነ ለወዴቻው ክብር ተብሎ የልጅቷ ቤተሰቦች የቀረበላቸውን የጋብቻ ጥያቄ በሙሉ ፈቃደኝነት እንደሚቀበሉ ይነገራል። የዋንዛ በትር በቱለማ ኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ አብላጫውን ጊዜ በሚያስብል ሁኔታ ለጋብቻ አንዲት ልጃገረድን ከማጨት፣ የጋብቻ ጠያቂና አስፈፃሚ ከሆኑ ሽማግሌዎች የልመናና የማግባባት ምልልስ፣ ከጋብቻ ዕለት ስነስርዓት እና ከአግቢው ግለሰብ ጋር የተዛነቀ ነው።

በሰርጉ ዕለት ወዴቻ ይይዛል። ወዴቻ ከአግቢው ወንድ ሙሽራ ጋር የሚያያዝበት ምክንያት ሴቷ ሙሽራ ሲንቄ እንደምትይዝ ሁሉ እርሱም የዋንዛ በትር መያዝ የሚጠበቅበት በመሆኑ ነው። ስለሆነም በገዳ ሥርዓት ውስጥ በተለይም ለባህሉ ቅርበት ባለው ኅብረተሰብ ዘንድ ያገባ ወንድ በሙሉ በነፍስ ወከፍ ወዴቻ ይኖረዋል። በዚህ ረገድ ወዴቻ ያገባ ወንድ ትዕምርት ነው፤ ግለሰባዊ ምልክትም ነው። የርዕስ ጉደዩ ሃሳብ ሲጠቃለል ወዴቻ የያዘ ሰው፦ሚስት ያገባ መሆኑን፣ በገዳ ሥርዓት ከበራ ላይ መሳተፉን፣ ኃይማኖታዊ እና መንፈሳዊ ተግባራትን መፈፀሙን፣ የሕዝቡን ባህልና ወግ የሚያውቅ መሆኑን፣ ሰዎችን ለማስታረቅ፣ የጋብቻ ጥያቄ ለማቅረብ ከሚላኩ ሽማግሌዎች አንዱ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይችላል (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ)።

ወዴቻ እና አባ ወዴቻ ዕርቅ ለማከናወን፣ ሰላም ለማስፈንም ከፍተኛ ሚና አላቸው። በትንታኔውም ሆነ በመረጃ አቀባዮች ምላሽ ውስጥ እንደታየው ከተዘረዘሩት የከበሩ ንዋያት ጋር ለዕርቅ መከወኛ የሚያገለግሉ ተዛማጅ የሆኑ ግብዓቶችም አሉ። ከጥናቱ መጠነ ርዕይ አንፃር ሁሉንም በዚህ መጣጥፍ ውስጥ መተንተን ባይቻልም በዕርቅ ከበራ ላይ በተደጋጋሚ የሚቀርቡትን ውስን ጉዳዮች መርጠን የትንታኔው አካል አድርገናል። ከነዚህም መካከል በዕርቅ ወቅት የዕርቅ ምልክት የሆነው እሬቻ፣ ከጉማ ስነስርዓት ጋር ተያይዞ ብዙውን ጊዜ በክዋኔ ላይ የሚገኙት ፈረስ እና ድፍን ቅል ተጠቃሽ ናቸው። ትዕምርታዊ ፍቺያቸው እንደሚከተለው ተመልክቷል።

***ሠ. ፈረስ/* Farda: -** በኦሮሞ ባህል ውስጥ ትልቅ ግምት እና ቦታ ይሰጠዋል፤ በቱለማ ኦሮሞ ዘንድም ፈረስ ተወዳጅ የሆነ የቤት እንስሳ ነው። በተለይ ለጉማ ሥርዓት እና ለጉግስ ውድድር ወዘተ. ትላልቅ ጉዳዮች ላይ የሚውል ፈረስ በልዩ ስሙ ጮሌ ይባላል። ፈረስ በኦሮሞ ዘንድ የተከበረ ነው፣ *"Fardi Oromoo biratti ulfaadha. Collee jedhama. Oromoon Farda inkabaja. Fardi ayyaantummaa qaba jadhamee yaaddama. Moonaa keessayyuu Farda qabaachuun nama horsiisa, milkii qaba jedhama* - ፈረስ በኦሮሞ ዘንድ ክቡር (የከበረ) ነው። ጮሌ ይባላል። ኦሮሞ ፈረስን ያከብራል። ፈረስ መንፈሳዊነት አለው ተብሎ ይታሰባል። ከበረት ፈረስ ካለ እንኳ ለእርባታ መልካም ነው፤ ገድ/ሚሊኪ አለው ይባላል" (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ)። በተመሳሳይ ታቦር (2007ዓ.ም፡140) ፈረስ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ያለውን ክብር እና ሚና እንዲህ ይገልፃል፣

> *ከጥንት ጀምሮ ፈረስ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ትልቅ አክብሮት አለው። ፈረስ ለጌታው ታማኝ ነው፤ ሰው ከላዩ ላይ ቢወድቅና መነሳት ቢያቅተው አብሮ እዚያው ቆሞ ድምፅ እያሰማ ይውላል ወይም ያድራል እንጂ ጥሎ አይሄድም፤ ፈረስ በልጓም ተለጉሞ ሲለመን እግዚአብሔር ይሰማል፤ ፈረስ አይገደልም፤ የሚሉ አባባሎች በስፋት የሚደመጡት በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ነው። ለምሳሌ ሰው በእጃቸው የሞተ/የጠፋ ወገን ሰላም እንዲፈጠር፤ ተበዳዩን ወገን ለአጸፋ መልስ ከመዘጋጀቱ በፊት ሽማግሌዎችን ይልካል። ሽማግሌዎቹንም ለአቤቶታ ሲልኩ ከለቻ እና ጫጩ አሲዘው ከተለጎመ ፈረስ ጋር አድርገው ነው።*

በተገለፀው መሠረት በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ለፈረስ ጉግስ ውድድር፣ ከቦታ ቦታ ለመጓጓዣነት… ከሚሰጠው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት በተጨማሪ የሰላም እና የፍቅር፣ የተወዳጅነት እና የክብር፣ የጀግንነት እና የመንፈሳዊነት፣ የታማኝነት እና የዕርቅ ምልክት ነው፡፡ ልዩ እንክብካቤም ይደረግለታል፣ "ፈረስ ለሰው ከሚሰጠው አገልግሎት አንፃር ካሉት እንስሳት የተለየ እንክብካቤ ይደረግለታል፡፡ ስለዚህ አምላክ ፈረስን ልዩ አድርጎ ለሰው ልጅ የፈጠረው ነው ይባላል፡፡ እንዲህም በመሆኑ ፈረስ ተለጉሞ በእግዚኦታ አውዳዊ ክዋኔ ላይ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ይህን ማድረጉ ደግሞ የተጣሉትን ለማስታረቅ፣ የሚቼ ወገኖች እርቁን እንዲቀበሉ ለማድረግ ይረዳል ተብሎ ይታመናል (ሙሉጌታ፣ 2007ዓ.ም፡ 72)፡፡ በዚህም ሳቢያ ፈረስ በተይም በጉማ ስነስርዓት ላይ ተለጉሞ ይቀርባል፡፡ ፈረስ ለጉመው እርቅ የሚጠይቁት የገዳይ ወገን ናቸው፡፡ ፈረስ የመለጎሙም ምክንያት ላጠፋነው ጥፋት አንደበት የለንም፤ አንደበታችን ልክ እንደፈረሱ ተለጉሟል የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑን ከመረጃ አቀባዮች ከተገኘው መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም "በኛም ሆነ በተለጎመው ፈረስ አትጨክኑ ታረቁን" የሚል መልዕክት ያዘለ ነው፡፡ በባህሉ መሠረት ፈረስ ካለው ክብር የተነሳ የሚች ወገኖችም ልጓሙ እንዲፈታ፣ የዕርቅ ስነስርዓቱም እንዲጀመር እና ሂደቱም እንዲቀጥል ፈቃዳቸውን ያሳያሉ፡፡ ምክንያቱም ከለቻ፣ ጫጩ እና የተለጎመ ፈረስ ለዕርቅ ወጥተው እምቢ አይባልም፡፡ ስለሆነም በዕርቅ ተምሳሌትነቱ በእጅጉ የላቀ ነው፡፡

## ረ. ድፍን ቅል

ድፍን ቅል በተፈጥሮ የሚገኝ ተክል ነው፡፡ በውስጡ ሰፍነግ ያለው በመሬት ወይም በአጥር ላይ የሚንሰራፋ የተክል ዓይነት ነው፣ "በውስጡ ትናንሽ የፍሬ ዘር የያዘ፣ ክብና ውስጠ ክፍት የሆነ ትልቅ ፍሬ የሚጥል ወይም የሚያፈራ፣ መሬት ላይ ተንሰራፍቶ ወይም በአጥርና በዛፍ ላይ እየተንጠለተለ የሚያድግ ሃረግማ የተክል አይነት፤ ውሬውም ቅል ይባላል (የኢ.ቋ.ጥ. ም.ማ፣ 1993፡ 179"፡፡

በጉማ ሥርዓት የዕርቅ ክዋኔ ወቅት ድንግል የሆነች ታዳጊ ሴት ድፍን ቅል ይዛ ትገኛለች፡፡ በባህሉ መሠረት የራሱ ትርጉም፣ የራሱ ትዕምርታዊ ፍቺ አለው፣ *"Dubarri duudaa kabaja qabdi; hineerumne. Buqqeen duudaanis akkasumatti ilaallama. Garaa keessaaa sanyii qaba; Akkuma dubra duudaa san iccitiin isaa hinbeekkamne. Akka Waaqni umetti jira. Buqqee kana Oromoon akka hoodaatti ilaala* - ድንግል ሴት ክብር አላት፡፡ ድፍን ቅልም እንዲሁ ይታያል፡፡ በውስጡ ዘር አለው፤ አልተበሳም፡፡ እንደ ድንግሏ ልጅ ምስጢሩ አልታወቀም፡፡ እግዚአብሔር እንደፈጠረው ነው ያለው" (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ)፡፡

ድንግልና በተፈጥሮ የሚገኝ ነው፡፡ "ክብረ ንፅህና" እንዲሉ - በባህሉ መሠረት ከንፅህና እና ከቅድስና ጋር ይያያዛል፡፡ ቅልም እንዲሁ በተፈጥሮ የሚገኝ እና በተፈጥሮ ያለ ነው፡፡ አልተነካም፡፡ ነገር ግን በህይወት ዑደት ውስጥ ሁለቱም ዘርን (የዘር ፍሬን) ከማስገኘት፣ የትውልድ ሀረግን ከማስቀጠል ጋር ትስስር አላቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በወካይነት እና በትዕምርታዊ ትጓሜ የሚቀርቡ ይመስላል፡፡

***ሸ. እሬቻ/ Irreecha: -*** *እሬቻ አንድም ለዋቃ የሚቀርብ ምስጋና/ ፀሎት ሲሆን አንድም የዕርቅ ምልክት የሆነውን ለምለም ሣር… ይወክላል፡፡ በዚሁ አግባብ ለዋቃ ምስጋና ማቅረቢያ እና የዕርቀሰላም ማስፈፀሚያ ግብዓት የሆነው እሬቻ (ለምለም ሣር) የዕርቅና፣ የሰላም ምልክት ነው፣*

> *እሬቻ በኦሮሞ ዘንድ የእርቅ ምልክት ነው፡፡ አንድ ሰው እሬቻ ይዞ ወዳንተ መጣ ማለት፣ ታረቀኝ ማለቱ ነው፡፡ በእሬቻ ሰላም ተባባልክ ማለት መታረቅ ማለት ነው፡፡ ወደ መልካ (ወንዝ፣ ሀይቅ) እሬቻ ይዘው ከሄዱ፣ እግዚአብሔር ሆይ ታረቀን" ማለት ነው፡፡ በዓለም ላይ እርግብ የሰላም ምልክት ናት፤ በኦሮሞ ዘንድ የሰላም ምልክት እሬቻ ነው እንጂ እርግብ አይደለም (አቶ ማሞ ገዳ፣ 08/12/2011 ዓ.ም አዳማ - በትርጉም የቀረበ)፡፡*

*በዚሁ የዕርቅ እና የሰላም እሳቤ የእሬቻ[24] በዓል ስነስርዓት ከመካሄዱ በፊት የተጣሉ፣ የተኮራረፉ የተቀያየሙ እና የማይነጋገሩ ሰዎች በችግሮቻቸው ዙሪያ ተነጋግረው ዕርቅ ያወርዳሉ፡፡ ነገር ግን በኦሮሞ ባህልና የገዳ ሥርዓት መሠረት የሰው ልጅ በልቡ ክፋት፤ ምቀኝነት፣ ቂምና በቀል፣ ጥላቻና ቅሬታን ይዞ ለምስጋናም ሆነ ለፀሎት ከፈጣሪው ፊት መቆም የለበትም፤ በንፁህ ልብ ያልተፈፀመ ምስጋናና ፀሎትም በፈጣሪ ዘንድ ተሰሚነት እና ተቀባይነት የለውም ተብሎ ይታሰባል፡፡*

*በእሬቻ በዓል ላይ የሚታደሙ ሰዎች እርስ በርሳቸው ፍቅርና አንድነትን ሳይመሰርቱ የእሬቻን ሣር አብረው የማይዙበት ዋናው ምክንያት ሰላም በሌለበት የሰላም ምልክት የሆነውን ለምለም ሣር አብሮ መያዝ ከእሬቻ መሠረታዊ መርሆ ጋር ስለሚጣረስ ነው፡፡ ስለሆነም በተለያዩ ምክንያቶች የተጣሉና የተቀያየሙ ሰዎች የእሬቻ በዓል ከመድረሱ በፊት ይቅርታ መጠያየቅ፣ አንዱ ለሌላው ይቅርታ ማድረግ፣ ዕርቅ ማውረድ፣ ቂምና በቀልን በመተው ሰላምን ማስፈን፣ ከልብ በመነጨ ይቅርታ እርስ በርስ መዋደድ፣ መከባበርና መደማመጥ የመጀመሪያው መስፈርት ይሆናል፡፡*

*በዚሁ መሠረት የኦሮሞ ህዝብ በተለያዩ ጊዜያት በሚካሄዱ የገዳ ከበራዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ኃይማታዊና ማህበራዊ አጋጣሚዎች ዕርቅ እየፈጠረ ይሄዳል፡፡ ይህ ደግሞ ትናንሽ የሆኑ ፀብ እና ቁርሾዎች ወደ ተካረረ ግጭት እንዳያመሩ፣ በአጭሩም እንዲቀጩ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የዕርቅ ስነስርዓቱም የግጭት አፈታት ዓይነቱ በሚጠይቀው የተለመደ አካሄድ መሠረት ይከወናል፡፡*

---

24 በሌላ በኩል (ጥላሁን 2007፣126-131) "እሬቻ  እንደ ማስፈቀጃ"፣ "ገንዘብ እንደ እሬቻ፣ "እንደ ገንዘብ"፣ "እሬቻ እንደ ደረጃ ማስጠበቂያ"፣ "እሬቻ እንደ ማስገደጃ "፣ "እሬቻ እንደ ሰላም ወይም ሰላም ፈላጊነት" በማለት የእሬቻ አገላለፅና አተገባበር በማኅበረሰቡ ዘንድ የተለያየ መልክ እንዳላቸው በዝርዝር ተንትነዋል

## 5. ማጠቃለያ እና የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት "ዕርቀሰላም፡- የቱለማ ኦሮሞ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስልት መቋጫ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የቱለማ ኦሮሞ የግጭት አፈታት ሂደት ከገዳ ሥርዓት ጋር የተሰናሰለ መሆኑን በትንታኔ አሳይቷል። የኦሮሞ ህዝብ ለአያሌ ዓመታት በገዳ ሥርዓት ሲተዳደር ስለመቆየቱ የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ። የገዳ ሥርዓት የህዝቡ መለያ እና መታወቂያ ከመሆኑም ሌላ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ኃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ህይወቱንም ጭምር አካቶ የያዘ ባህላዊ አስተዳደር ነው (Asmerom, 1973; Taddesse, 2018; ድርቢ፣ 2007ዓ.ም፤ ዓለማየሁ፣ 2000ዓ.ም)። የህዝቡን ሁለንተናዊ ህይወትም ከገዳ ሥርዓት ውጪ ነጥሎ መመልከት አስቸጋሪ ነው፣ "የኦሮሞ ሁለንታናዊ ሕይወት በየትኛውም አቅጣጫ ምሉዕ በሆነ መልኩ ሊጤን የሚቻለው በገዳ ሥርዓት ውስጥ መመዘን ሲችል ነው" (ዝኒ ከማሁ፣ 2000ዓ.ም፡ 79)።

በገዳ ሥርዓት ውስጥ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዓብይነት ጉዳዮች አንዱ በሀገር በቀል ዕውቀት ላይ የተመሠረተው የግጭት አፈታት ነው። የገዳ ሥርዓት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በጥናቱ ትንታኔ መሠረት በማህበረሰቡ ግንኙነት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ግጭት ሊከሰት ይችላል። ግጭት የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮ አካልም ነው። በገዳ ሥርት መሠረት ዕርቅ እና ሰላምን ማስፈንም ያንኑ ያክል የዘውትር ተግባር ነው። ገዳ ለዕርቅና ሰላም ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በቱለማ ገዳ ሥርዓት መሠረት ዕርቅ በጊዜ ያልተገደበ ነው። ይኸውም ዕርቅ የሚፈፀመው በተለመዱት የሽምግልና፣ የሸነቻ፣ የቂጤ እና የጉማ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ኃይማኖታዊ አጋጣሚዎች እንደ የመስቀል በዓል፣ እሬቻ፣ የፈረስ ጉግስ፣ የደቦ ሥራዎች፣ የዋቄፈና እና የገዳ ክብረ በዓላዊ ክዋኔዎች ወቅት ነው። ክብረ በዓላቱ ከመድረሳቸው አስቀድሞ እና ከተከበሩ በኋላም በከበራ ላይ በተፈጠሩ አለመግባባቶች ዙሪያ ሁሌም ዕርቅ ይከናወናል። ችግሮችም ወዲያውኑ ይቋጫሉ፤ መፍትሔም ያገኛሉ። የዚህ ጥናት ጭምቅ ሃሳብ የሚያጠነጥንበት ዋናው ቁምነገር ግጭት ወደ ከፋ ደረጃ ሳይደርስ፣ ሰብዓዊ እና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ድርብርብ ቀውሶችን ሳያስከትል በሰከነ ብልሃት ቶሎ ብሎ መፍታቱ ላይ ነው። በገዳ ሥርዓት መሠረት ይቅርታ መጠየቅም ሆነ ይቅርታ ማድረግ የአንድ ሰሞን ክስተት ብቻ ሳይሆን የሁልጊዜ ኩነት ነው። በገዳ ሥርዓትም ሆነ በማህበራዊው ህይወት ውስጥ ህዝቡ ዕርቅ ለመፍጠር፣ ግጭትን ለማስወገድ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ሂደት ውስጥ የከበሩ ንዋያት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በትንታኔው ውስጥ ተገልጿል። በቀልን፣ መገዳደል እና መጠፋፋት እንዳይስፋፋ በመከላከል ረገድ የተገዳደሉ ሰዎች ጭምር ዕርቅ ፈጥረው፣ በአንድ ማዕድ በልተው፣ በአንድ ገበያ ተገበያይተው፣ አብረው እያወጉ ተመልሰው፣ ውለውና አድረው፣ ተጋብተው፣ ተዋልደው እና ተዛምደው በፍቅር እና በሰላም ለመኖር ሁነኛ መፍትሔ እንደሆኑ ከጥናቱ ማጠቃለያ እና ግኝት መረዳት ይቻላል። ይህ ዓይነቱ የቱለማ ኦሮሞ የግጭት አፈታት በአንዳንድ አካባቢ እንደሚታየው እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ለሚዘልቀው ተከታታይ መገዳደል - "ጥቁር ደም" መፍትሔ ይሆናል። ይህም ዕርቅ

በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለውን እውነተኛ ፍርድ እና ማህበራዊ ፍትህን፣ እኩልነት እና የህግ የበላይነትን ተግባራዊ በማድረግ፣ ግጭቶችንም አስተማማኝ በሆነ መልኩ በመፍታት እና በመቋጨት ዘላቂ ሰላምንም ያሰፍናል፡፡ ያወርዳል፡፡

በጥናቱ የታየው የኦሮሞ የግጭት አፈታት በአምስት ምሶሶዎች (Pillars) ላይ የተዋቀረ ነው፡፡ እነርሱም 1ኛ. የተጣሉ ሁለት ሰዎች (ወገኖች) በሚፈልጉት እና በመረጡት ሽማግሌ የመዳኘት መብት፣ 2ኛ. የሽማግሌዎች (ሽምጋዮች) ገለልተኛ መሆን፣ 3ኛ. ያለምንም ሙስና (ጉቦ) እውነትን ማዕከል አድርጎ የተከሰተውን ሀቅ ፈልፍሎ ማውጣት፣ 4ኛ. ተካሰው ወይም ከቀረቡት ሁለት ሰዎች ማን እውነተኛ (ተበዳይ)፣ ማን ጥፋተኛ (በዳይ) እንደሆነ መለየት እና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ በዳይ ተበዳይን እንዲክስ ማድረግ፡፡ 5ኛ. ሁለቱም ወገኖች ዳግም ወደዚህ መጥፎ ድርጊት እንዳይመለሱ ተመክረው እና ቃል ገብተው የዕርቅ ስነስርዓቱን ማከናወን (ዕርቅ ማውረድ) ነው፡፡ በዝርዝር የቀረቡት ሃሳቦች የቱለማ ኦሮሞ የግጭት አፈታት ስልት ውስጥ ከዕርቅ በኋላ በፍቅር እና በሰላም አብሮ ለመኖር የሚያግዙ መሠረታዊ ነጥቦች ናቸው፡፡ በመተማመን ላይ የተመሰረተው ይህ ዕርቅ በቀላሉ አይፈርስም፤ ባለመፍረሱም ለዘላቂ ሰላም ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ ካለምንም ተፅዕኖ እና አድሎ… በእውነት ላይ ብቻ ተመስርቶ መነጋገር፣ መወያየት እና መፍትሔ መሻትም በትንሽ በትልቁ ምክንያት የማይናወጥ ዕርቅ ለመፈፀም ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡ እንዲህም በመሆኑ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ይልቅ እውነተኛ ዕርቅ ይፈፀምበታል ተብሎም ይታሰባል፡፡ በብዙ መልኩም ተመራጭ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በመደበኛው የመንግሥት ፍርድ ቤት የሚታየውን የቀጠሮ ምልልስ ለማስቀረት፣ አንድ ጉዳይ በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት እንዲያገኝ በማድረግ ለምግብ፣ ለአልጋ፣ ለትራንስፖርት ወዘተ. የሚወጣውን ወጪ በመቀነስ፣ በደል ፈፃሚው በማረሚያ ቤት ለረዥም ጊዜ እንዳይቆይና በዚህም ምክንያት ቤተሰብ እንዳይበተን… የገዳ የዳኝነት ሥርዓት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ወጪ ቆጣቢና እውነተኛ ፍትህን የሚያስገኝ ከመሆኑም በተጨማሪ የመልካም አስተዳደር ምሳሌ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሱት የከበሩ ንዋያት (Ulfaalee) በዕርቅ አፈፃፀም ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በከበሩ ንዋያቱ የተከናወነ ዕርቅ ክህደትም፣ ቅጥፈትም አይኖረውም፤ በትናንሽ እና በቀላል ምክንያቶችም አይፈርስም፡፡ ዘላቂ ነው፤ የፀና ነው፡፡ በትዕምርታዊ ፍከራቸውም (Symbolic Interpretation) የህዝቡን የዓለም አተያይ እና ፍልስፍና የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከለቻ የወንዶችን ክብር፣ ጫጩ የሴቶችን ክብር የሚገልፁ የከበሩ ንዋያት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም ምክንያት ቦኩ እና ከለቻ ወንዴ ፆታን፤ ጫጩ ሴቴ ፆታን፤ መራባትን፣ እውነትን፣ ፍትህን፣እኩልነትን እና ሰላምን… ይወክላሉ፡፡ የዕርቅ ማዕዶቹም ሆኑ በአስታራቂነት የሚሰየሙት ሽማግሌዎች የእውነት ተምሳሌት ናቸው፡፡ የኦሮሞ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስልቶች ዋና ማጠንጠኛቸው እውነት፣ ግባቸውም ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ነው፡፡ ከህብረተሰቡ ህይወት ጋርም የጠበቀ ትስስር አላቸው፡፡

በዚሁ መሠረት በኅብረተሰቡ ዘንድ ዕርቀሰላምን ለማስፈን ባህላዊ የሽምግልና፣ ሸነቻ፣ ሰግሊ፣ ቂጤ እና የጉማ ሥርዓት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው በዚህ ጥናት

ተመልክቷል፡፡ እነዚህን የግጭት አፈታት ስልቶች ውጤታማ ለማድረግ የከበሩ ንዋያቱ የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ ይልቁንም የጉማ ሥርዓትን ካለ ከለቻ እና ጫጩ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ የሀገር በቀል እውቀት ውጤት የሆኑት እነዚህ የከበሩ ንዋያት ከገዳ ሥርዓትና ከዋቄፈና እምነት ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸው ሲሆን ግጭትን ለማስወገድ፣ ዕርቅና ሰላምን (Araara fi naga'a) ለማስፈን፣ ማኅበራዊ ቀውሶችን ለመቀነስ፣ ብቀላና ግድያን ፍፁም ወደሆነ ዝምድና ለመቀየር ወሳኝ ድርሻ እንዳላቸውም የጥናቱ ውጤትና ግኝት ያመለክታል፡፡

## 6. ይሁንታ

በቀረበው ትንታኔ የቱለማ ኦሮሞ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስልት ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን የጎላ ሚና እንዳለው ተመልክቷል፡፡ በማንኛውም ጊዜ የሚካሄድ ዕርቅ ገለልተኝነትን፣ እውነትን፣ ትክክለኛ ፍርድ እና ፍትህን፣ የበደለ የሚክስበትን፣ የተበደለ የሚካስበትን፣ በመሸነጋገል ሳይሆን ከልብ በመነጨ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ዕርቅ በመፈፀም ሰላምን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡ ይህን አይነቱን ግልፅነት እና ተአማኒነት ያለውን የዕርቅ ሂደት መከተልም ችግሮችን በሰላማዊ ሁኔታ ለመቋጨት፣ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የላቀ ፋይዳ ስላለው ለሀገር በቀል የግጭት አፈታት ተገቢውን ክብር እና ቦታ መስጠት ይገባል፡፡ ግጭቶች ውለው ሳያድሩ፣ ችግሮቹም ሳይወሳሰቡ ወዲያውኑ ከስር ከስር የመፍታት እና እልባት የመስጠት አካሄድን ከባህላዊው የቱለማ ኦሮሞ የግጭት አፈታት ስልት ልምድ መቅሰም ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ሀገራችን አሁን ያለችበት ወቅታዊ ሁኔታ ውይይትን፣ ዕርቅና ሰላምን የሚያሻት ታሪካዊ አጋጣሚ ላይ የምትገኝ በመሆኗ ሀገር በቀል የሆነውን የግጭት አፈታት በአማራጭነት መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ በዚህም መሰሉ ሂደት የከበሩ ንዋያቱን በተለይ በኦሮሚያ ክልል ደረጃ ለሚካሄድ ዕርቅ መጠቀም አስተማማኝ ሰላምን ለማስፈን የላቀ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ እነዚህ የከበሩ ንዋያት እንደ የዕርቅ ተቋማት የሚታዩ የሀገር በቀል ውጤት ናቸው፡፡ ስለሆነም የከበሩ ንዋያቱን በቅርስነት መመዝገብ፣ ሙዚየም በመክፈት የቱሪስት መስህብ እና የገቢ ማስገኛ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ከከበሩ ንዋያቱ ጋር ተያይዞ እየታየ ያለው ለውጥ ፈጣንም አሳሳቢም ስለሆነ በውስጣቸው የያዙትን ትዕምርታዊ ፍቺ እና አገልግሎታቸውን በተመለከተ ለአዲሱ ትውልድ ማስተማር፣ አዲሱን ትውልድ በግብረገብነት እና ስነምግባር ማነፅም ሁሌም ቢሆን ቸል የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ ገዳን ጨምሮ በሌሎች አካባቢ የሚገኙ የሀገር በቀል እውቀቶችን የሚያጠና፣ የሚያስተባብርና የሚተገብር የሀገር በቀል እውቀት ማዕከል በክልል፣ በዩኒቨርሲቲና በተለያዩ ተቋማት እንዲሁም ማዕከላቱን የሚመራ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ማቋቋም የመንግሥትና የተቋማቱ ኃላፊነት ነው፡፡ ለተግባራዊነቱም ፖለቲከኞች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ ባህል ሚኒስቴር፣ የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ ትምህርት ሚኒስቴር በጥቅሉም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ ጥናቱን የሚረከበው ዩኒቨርሲቲ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡

## ማጣቀሻዎች

ሕዝቅያስ አሰፋ፡፡ 2011ዓ.ም፡፡ *የሰላምና ዕርቅ ትርጉምና መንገዶች፡፡* አዲስ አበባ፣ Don Bosco Printing፡፡

ሙሉጌታ ነጋሣ፡፡ 1997ዓ.ም፡፡ "በአደኣ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ያልታተመ፡፡

ሰለሞን ተሾመ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ *ፎክሎር፡ ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ኃላ/የተ/የግ/ ማህበር፡፡

ስንቅነሽ አጣለ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ "ባህልና ልማት በበርታ ብሔረሰብ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: ለዶክተሬት ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ፡፡

ብሩ ጸጋዬ፡፡ 2008 ዓ.ም፡፡ *የሥልጣኔ አፍሪካዊ ምንጭና በተረት መጋረጃዎች የተደበቁ እውነቶች፡፡* ኢትዮጵያ፣ አዳማ ድር ማተሚያ ቤት፡፡

ቀነዓ ለሚ፡፡ 2010 ዓ.ም፡፡ "የኦሮሞ ሚቶሎጂ ይዘታዊ ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ፤ አአዩ: ለዶክትሬት ድግሪ ማሟያ፤ ያልታተመ፡፡

ታቦር ዋሚ፡፡ 2007 ዓ.ም፡፡ የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች (3ኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ኃይለገብርኤል ዳኜ፡፡ 2007ዓ.ም፡፡ ባህልና ትምህርት በኢትዮጵያ፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ዓለሙ አማረ፡፡ 2009ዓ.ም፡፡ የግጭት አፈታትና አያያዝ ጥበብ፡፡ አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም)፡፡

ዓለማየሁ ኃይሌ እና ሌሎች፡፡ 2000 ዓ.ም፡፡ በገዳ ሥርዓት የቱለማ ኦሮሞ ፖለቲካ፡፡ ኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ (ኦ.ባ.ቱ.ቢ)፣ *ፊንፊኔ*፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የራስወርቅ አድማሴ፡፡ 2004ዓ.ም፡፡ *ባህልና ልማት፡- ምንነታቸውና ትስስራቸው፡፡ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ*፤ ፎረም ፎር ሶሻል ስቴዲስ (አሳታሚ)፣ ሽፈራው በቀለ (አርታኢ)፣ አዲስ አበባ፣ Printed @ Eclipse፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ 1993 ዓ.ም፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

Asmerom Legesse. 1973. *Geda፡ Three Approaches to the Study of African Society*. New York: the Free Press.

Blaxter, L. 2006. *How to Research.* England: Open University press.

Bloor, M. and Wood, F. 2006. *Key Words in Qualitative Method*. London: SAGE publications.

Charon, Joel M. 1989. *Symbolic interactionism*. New Jersey: Prentice Hall.

Cirlot, J.E.1971. *A Dictionary of Symbols*. London: Rutledge.

Danesi, Marcel. 2004. *Messages, Sings, and Meanings: A Basic Textbook in Semiotics and Communication Theory (3edi).* Toronto: Canadian Scholars Press.

Dejene Gemechu. 2002. "Some Aspects of Conflict and Conflict Resolution among Waliso Oromo of Eastern Mecha, with particular Empasis on the Guma**".** M.A. Thesis in Social Anthropology, Addis Ababa University.

Dirribii Damissee. 2016. *Ilaalcha Oromoo፡Barroo Aadaa, Seenaa fi Amantaa Oromoo*. Finfinnee. Saabaa publishing.

Eskedar Girum. 2008. "Traditional Conflict Management Institutions among Aleltu Oromo Community, Northern Shewa, Ethiopia". MA. Thesis in Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

Geertz, Cliford. 1993. *The Interpretation of Cultures: Selected Essays*. New York: Basic Books, Inc.

Hornbay. AS. 2010. *Oxford Advanced Leaner's Dictionary*. New York, Oxford University Press.

Maammoo Gadaa. 2002. *Duudhaa*. Finfinnee: MYBT Printing Press.

Mack, N. 2005. *Qualitative Research Methods: A data Collector's Filed Guide.* USA: Family Health International (FHI).

Melaku Abera. 2010. "Land disputes and disputes Settlment mechanisms among the Tulama Oromo of Sululta district, Northern Shewa". M.A Thesis in Indigenous Cultural Studies, Addis Ababa Univrsity.

Mertens, Donna M. 2015. *Research and Evaluation in Education and Psychology. (4th Edition.)* SAGE publications.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. 2011. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. Utah State University Press.

Smeets, Rene. 1982. *Signs, Symbols and Ornaments*. New York: Van Nestrand Company.

Taddesse, Berisso. 2018. "The Oromo Gadaa System: Why Considered Democratic?" *Gadaa Journal*, Vol. 1, No 1.

Turner, Victor. 1967. *The Forest of Symbols: Aspects of Ndembu Ritual.* United Kingdom; Cornell University Press.

Tylor, Edward B. 1993. *Primitive Culture; Researches into the development of mythology, philosophy, religion, language, art, and custom (Vol.1).* London: Murray.

UNEP. 2008. *Indigenous Knowledge in Disaster Management in Africa*. Kenya.